# በፍትህ አካላት ማሠልጠኛ ተቋም

# ለቅድመ-ሥራ ሠልጣኞች

## በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ

## ላይ ለተዘጋጀው የሥልጠና ማኑዋል ለማሳያነት የቀረበ የአጠቃቀም መመሪያ

**አዘጋጆች፦ አሠግድ አያሌው**

**ፀጋዬ ወርቅአየሁ**

**ነሐሴ 25 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ምዕራፍ አንድ**

አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-

1. የወንጀል ስነስርአት ህግን የሚመለከቱ የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች ይለያሉ

2. የወንጀል ስነስርአት ህግ ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በማስከበርና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በኩል ስላለው ሚና ይረዳሉ።

3. የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግን ተግባራዊ በማድረግ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸምና የትርጉም ችግሮችንና ይለያሉ፣ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል ወጥ፣ ተገማችና ተመራጭ የሆነ ትርጉም ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ይኖራቸዋል።

4. አስቸጋሪ ጉዳዮችን በተመለከተ በቀላሉ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ክህሎት ያዳብራሉ።

**ክፍል አንድ**

ይህ ክፍል በአጠቃላይ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ምንነት አስፈላጊነት እንዲሁም ከሕገ መንግሥቱ ጋር ስላለው ቁርኝት ገለፃ የሚደረግበት ሲሆን አሠልጣኙ በርዕሰ ጉዳዮቹ ዙሪያ በሥልጠና ማኑዋሉ በሰፈረው ሁኔታ (ከተቻለም በሰፋ ሁኔታ ማብራሪያ ሰጥቶ በክፊለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ በሰፈሩት ጥያቄዎች ላይ ሠልጣኞች እንዲወያዩ ማድረግ ይጠበቅበታል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 10 ሰዓት)

**ክፍል ሁለት**

ከዚህ ክፍለ ትምህርት ጀምሮ በቀጣይነት ያሉት የዚህ ምዕራፍ ክፊሎች በአጠቃላይ የወንጀል ሥልጣንን ከተለያየ አቅጣጫ የሚዳስሱ ሲሆኑ በዚህ ክፍለ ትምህርት

- የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳይን ለማየት ሥላላቸው ሥልጣን
- በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ስለሚዳኙ ሰዎች
- ስለ ዋና ሥልጣንና ወሰኑ ስለ ምትክ ሥልጣን

በዋናነት በስልጠና ማኑዋሉ በተካተተው መሠረት በአሠልጣኙ መሪነት በሚደረጉ ገለፃዎችና በምሳሌነት በተቀመጡ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች መሰረት ክፍለ ትምህርቱ ይከናወናል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 6 ሰዓት)

**ክፍል ሦሥት**

በዚህ ክፍለ ትምሕርት በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተዘረዘሩ የወንጀል ጉዳዮች ላይ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ያላቸው የማየት ሥልጣን ይዳሰሳል። ለክፍለ ትምህርቱ ተብሎ ተለይቶ የተቀመጠ የመወያያ ጥያቄ ባይኖርም ክፍለ ትምህርቱ በአሠልጣኙ በሚደረግ ማብራሪያ ይመራል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ10 ሰዓት)

**ክፍል አራት**

በዚህ ክፍለ ትምህርት፡-

- የሥረ ነገር ሥልጣን (Material Jurisdiction)
- ክልላዊ ሥልጣን (Local Jurisdiction)

ለክፍለ ትምህርቱ የተቀመጡ ምሣሌዎችን ማጣቀሻ በማድረግ ውይይት እንዲደረግ ይጠበቃል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 4 ሰዓት)

**ምዕራፍ ሁለት**

አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-

1. የወንጀል ክሥ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የምርመራ መዝገብ በምን ዓይነት ሁኔታ መመራት እንዳለበት ይገነዘባሉ ተግባራዊም ያደርጋሉ
2. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ።
3. በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ።
4. ዋስትና ከሰብአዊ መብት ጋር ያለውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነቱ በጽናት ይሰራሉ፤
5. ዋስትና የሚፈቀድባቸው እና የሚከለከልባቸውን ምክንያቶች የተነትናሉ።

**ክፍል አንድ**

**መደበኛ የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት ውጤታማ የሆነ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ አመራር**

በዚህ ክፍለ ትምህርት ሰልጣኞች ለክፍለ ትምህርቱ በአጋዥነት የቀረበውን ቻርት መሰረት በማድረግ ለመወያየ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ይደረጋል አሠልጣኙ ማጠቃለያ ከሰጠ በኋላ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 12 ሰዓት)

__ክፍል ሁለት__

በዚህ ክፍለ ትምህርት፡-

- የጊዜ ቀጠሮ
- ዋስትና

በሚሉት ጉዳዮች ላይ በተዘጋጀው ማኑዋል መሠረት በአሰልጣኙ ማብራሪያ ይሠጣል፣ በተዘጋጁ የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ሠልጣኞች እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ አሠልጣኙ በሚሠጠው ማጠቃለያ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 10 ሰዓት)

__ክፍል ሦሥት__

በዚህ ክፍል በዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዛትና ውሣኔዎች አጠቃላይ ግባቸውና ይዘታቸው ምን መምሰል እንዳለበት አጭር ማብራሪያ በአሰልጣኙ ይሰጣል፣ ለማስተማሪያ በተመረጡት ጉዳዮች ላይ ሠልጣኞች እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ አሠልጣኙ በሚሰጠው ማጠቃለያ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 12 ሰዓት)

__ክፍል አራት__

የወንጀል ክሥ አቀራረብንና ክሥ ማሻሻልን የሚመለከቱ ችግሮች ላይ በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት አሰልጣኙ ገለፃ ያደርጋል፣ ለመወያያ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ሠልጣኞች እንዲወያዩበት ከተደረገ በኋላ አሰልጣኙ በሚሰጠው ማጠቃለያ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 12 ሰዓት)

__ምዕራፍ ሦሥት__

**አጠቃላይ ዓላማዎች፡-**

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-

1. ሙግትን ለመምራት የሚያስችል ክህሎት ያዳብራሉ፤
2. በሙግት አመራር ሂዳት የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ይረዳሉ፤
3. አማራጭ ሃሳቦችን ለማየት ይችላሉ፤
4. ቀልጣፋና ውጤታማ የሙግት አመራር ዘዴን ይረዳሉ፤

ዝርዝር አላማዎች፡-

- በችሎት አመራር ላይ የዳኛው ሚና ምን መሆን እንዳለበት ያውቃሉ፤
- የችሎት አመራርን በአግባቡ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ይረዳሉ፤
- ክስ መስማት ዝግጅትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ይችላሉ፤
- በክስ ዝግጅትም ሆነ በክስ መስማት ጊዜ የተከራካሪዎችን መብት ውጤታማ በሆነ መንገድ ያስፈጽማሉ፤
- የዕምነት ቃል አቀባበል ስርዓትን ይረዳሉ፤
- በምስክሮች አቀራረብ ረገድ ማን ኃላፊነት እንዳለበት ያውቃሉ፤
- በማስረጃ አቀባበል ሂደት በየደረጃዎቹ የተከራካሪዎች ሚና ምን መሆን እንዳለበት ይለያሉ፤
- አንድ ፍርድ ሊኖረው የሚገባውን ይዘት ያውቃሉ፤

በዚህ ክፍል አሠልጣኙ

- ስለ የክስ አሰማም ሂደት አጭር መግለጫ ለሠልጣኞች ይሰጣል፤
- የክስ መሰማት ዝግጅትን በተመለከተ በተለይ፡-

ክሥ የሚሰማበትን ቀን ስለማሳወቅ

ክሥ እና ማስረጃዎቹን ለተከራካሪዎች ስለማሳወቅ

- ክሡ ስለሚሰማበት ሁኔታ፣ አስተርጓሚ ስለመመደብ፣ ስለተከሣሽ አቀራረብ፣ ተከሣሽ በጠበቃ እንዲታገዝ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣ ስለመቃወሚያ፣ ክስን ስለመለወጥ ወይም ስለመጨመር፣ የተከሳሽን የዕምነት ክህደት ቃል ስለመቀበል፣ ስለዋስትና በስልጠና ማኑዋሉ መሰረት በአሰልጣኙ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

- ማስረጃና ፍርድን በተመለከተ በተዘጋጀው ማኑአል መሰረት በአሰልጣኙ ገለፃ ይደረጋል፡፡

በመቀጠልም ሰልጣኞች በተዘጋጁት የመልመጃ ጥያቄዎች ላይ በየቡድኑ እንዲወያዩ ይደረጋል፡፡

ከዚያም አሰልጣኙ በሚሰጠው ማጠቃለያ በምዕራፉ የተያዘው ርዕሰ ጉዳይ ይቋጫል፡፡

(ለክፍለ ትምሕርቱ የተያዘው ጊዜ 25 ሰዓት)

**ምዕራፍ አራት**

**አጠቃላይ ዓላማዎች፡-**

*ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-*

- የይግባኝ ሥርዓት መኖር ጠቃሚነቱን ይረዳሉ፣
- የይግባኝ ሥርዓት መኖር የተፈረደበት ወገን መብት (due process) ማስጠበቂያ መሳሪያ መሆኑን ያውቃሉ፣
- የይግባኝ መብት ወሰኖችን ያውቃሉ፣
- የይግባኝ ሥርዓት አመራርን ይረዳሉ።

*ሠልጣኞች ከትምህርቱ መጠናቀቅ በኋላ፦*

- የይግባኝ ትርጉምን ይረዳሉ፣
- የይግባኝ ሥርዓት መኖር በፍርድ ቤት አሠራር ላይ ዕምነት እንደሚያዳብር ይረዳሉ፣
- የይግባኝ ሥርዓት መኖር በፍርድ ሂደት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ይረዳሉ፣
- ይግባኝ የሚጠየቅባቸውን እና የማይጠየቅባቸውን ጉዳዮች ይለያሉ፣
- በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ይግባኝ ያልተፈቀደበትን ምክንያት ያውቃሉ፣
- ይግባኝ መቼ መጠየቅ እንዳለበት መናገር ይችላሉ፣
- የይግባኝ ማመልከቻ ሊይዛቸው የሚገቡ ፍሬ-ነገ ሮችን መለየት ይችላሉ፣
- የይግባኝ መስማት የሚከናወንበትን ሂደት ይረዳሉ።

በተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በተዘጋጀው የሥልጠና ማኑዋል መሰረት አሰልጣኙ ገለፃ ያደርጋል። በመጨረሻም በርዕሰ ጉዳዮቹ ዙሪያ በተዘጋጁት የመልመጃ ጥያቄዎች ላይ ሠልጣኞች በየቡድን እንዲወያዩ ከተደረገ በኋላ አሠልጣኙ በሚሰጠው ማጠቃለያ ምዕራፉ ይጠናቀቃል።

(በምዕራፉ ለተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች የተያዘው ጊዜ 15 ሰዓት)

**ምዕራፍ አምስት**

አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

*ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-*

1. በወንጀል ተጠርጣሪዎች እና በወንጀል ተጠቂዎች መካከል ያሉ ተነፃፃሪ መብቶችን ይገነዘበሉ
2. የወንጀል ተጠቂዎችን የሥነልቦናና ማህበራዊ ፍላጎቶች መሰረት ያደረገ የፍትህ አመራር ዘዴን ይለያሉ
3. ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ

<u>**ክፍል አንድ**</u>

በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለየወንጀል ተጠርጣሪዎችና የወንጀል ተጠቂዎች ተነፃፃሪ መብቶች በተዘጋጀው የስልጠና ማኑአል መሰረት በአሰልጣኙ ማብራሪያ ይሰጣል፣ በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ በቀረበው የመወያያ ጥያቄ ላይ ሰልጣኞች እንዲወያዩበት ከተደረገ በኋላ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

<u>**ክፍል ሁለት**</u>

በዚህ ክፍለ ትምህርት የወንጀል ተጠቂዎች በሚኖሩበት ወቅት ሊኖር ስለሚገባ የችሎት አመራር የሥልጠና ማኑአሉን መሰረት ባደረገ መልኩ አሰልጣኙ ማብራሪያ ይሰጣል፤ በመቀጠል ለመወያያ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ሰልጣኞች እንዲወያዩባቸው ከተደረገ በኋላ አሰልጣኙ በሚሰጠው ማጠቃለያ የክፍለ ትምህርቱ ማብቂያ ይሆናል።

(በምዕራፉ ለተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች የተያዘው ጊዜ 12 ሰዓት)

# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

## ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ሰልጣኞች የተዘጋጀ

## የስልጠና ሞጁል

# የወንጀል ሥነ-ሥርአት ህጎችና ሙግት መምራት

በፌደራል የፍትህ አካላት በለሙያወች ማሰልጠኛ ማእከል የተዘጋጀ

## የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጎችና ሙግትን መምራት

### ምዕራፍ አንድ

### የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጎች

አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ፡-

1. የወንጀል ስነስርአት ህግን የሚመለከቱ የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች ይለያሉ
2. የወንጀል ስነስርአት ህግ ህገመንግስታዊ ስርአቱን በማስከበርና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በኩል ስላለው ሚና ይረዳሉ፡፡
3. የወንጀል ስነስርአት ህግን ተግባራዊ በማድረግ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸምና የትርጉም ችግሮችንና ይለያሉ፣ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል ወጥ፣ ተገማችና ተመራጭ የሆነ ትርጉም ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ይኖራቸዋል፡፡
4. አስቸጋሪ ጉዳዩችን በተመለከተ በቀላሉ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ክህሎት ያዳብራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡-

በክፍለ ትምህርቱ የተመለከቱትን ንዑሳን ርዕሶች ከተማሩ በሃላ ሰልጣኞች፡-

1. የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉና ሕገ-መንግሥቱን ግንኙነት ይገልፃሉ
2. ከፍርድ ቤት ሥልጣን፣
3. የጊዜ ቀጠሮ አሰጣጥ፣
4. ዋስትና፣
5. በሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 38 እና 42 መሠረት የሚሰጡ መመሪያዎችን፣
6. የክስ አቀራረብና የክስ ማሻሻል፣

# ክፍል አንድ

## የወንጀል ሥነ ሥርዓትና ሕገ መንግሥቱ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

***ሠልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-***

- የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምን እንደሆነ ይተነትናሉ፤
- ሕገ መንግሥቱ እና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ያላቸውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነታቸው በፅናት ይሠራሉ፤
- በሀገራችን ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ህጎች ያብራራሉ፡፡
- የወንጀል ሥልጣን በፌዴራልና በክልል እንዴት እንደሚተገበር ተገንዝበው ለተግባር ይዘጋጃሉ

በዚህ ክፍል ውስጥ ዋና ዋና ፅንሰ ሃሳቦች ምን እንደሆኑ በቅድሚያ መታወቅ ስላለባቸው እንዲብራሩ ይደረጋሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ራሱ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው የሚለው ይዳሰሳል፡፡ ከዚህ ሌላ ማንኛውም በአንድ አገር ያለ ሕግ የሕጎች ሁሉ የበላይ ከሆነ ከሕገ መንግሥት አንፃር መታየት ስላለበት የሥነ ሥርዓት ሕጉና ሕገ መንግሥቱ ያላቸው ትስስርም አብሮ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

በታዋቂው ብላክስ የሕግ መዝገበ ቃላት ትርጓሜ መሠረት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት የሚከተለው ፍቺ ተሠጥቶታል፡-

> የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት የወንጀል ጉዳዮች የሚመረመሩበት፣ የሚከሰሱበት፣ የሚዳኙበትና የሚቀጡበትን መንገዶች የሚገዙ ደንቦች ናቸው፡፡ ይህም የተከሣሾችን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ጥበቃ ያካተተ ነው፡፡

ሕጎች በአጠቃላይ ከይዘታቸው አንፃር ዋና ሕጎች (Substantive Laws) እና ቅፅል ሕጎች (Adjanctive Laws) ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ መሠረታዊ ሕጎች የሚባሉት መብት፣ ግዴታ እና ተጠያቂነትን(liability) የሚመለከቱ ሲሆን፣ ቅፅል ሕጎች ደግሞ እነዚህ በሕግ ላይ የተመለከቱ መብት፣ ግዴታና ተጠያቂነት በአግባቡ በተግባር ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ የሚገዙ ናቸው፡፡ ቅፅል ሕጎች እንደገና የሥነ ሥርዓት (Procedural) እና የማስረጃ (Evidence) በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ከላይ ስለ ወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ትርጓሜ

ለመገንዘብ እንደሚቻለው ወንጀልን የሚያቋቁሙ መስፈርቶችን የሚደነግገው ዋናው የወንጀል ሕግን በሥራ ላይ የሚያውለው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ነው፡፡ ወንጀል ተፈፀመ ከተባለ በዋነኛነት በፖሊስ ምርመራ ይጣራል፣ በቂ ማስረጃ ከተገኘ በዐቃቤ ሕግ ክስ ይመሠረታል፣ ከዚያም ጉዳዩ በፍ/ቤት ታይቶ ጥፋቱ ከተረጋገጠ ተገቢው ቅጣት እንዲወሰን ይደረጋል፡፡

ወንጀል የሠራ እንዲጠየቅ ማድረግ የማኅበረሰቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ ቢሆንም ሂደቱ አጠፋ የተባለውን ሰው ሰብዓዊ መብቶች የሚጥስ መሆን የለበትም፡፡ የማኅበረሰቡን ጥቅምና የግለሰቡን መብት በተቻለ መጠን በሚያስታርቅ መልኩ ሕጉ ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዋና ዓላማም ይህ ዕውን እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ወንጀል ፈፃሚን ለይቶ አጣርቶ የማግኘት ሂደት በእጅጉ ከዜጎች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች መከበር ደግሞ ዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር በሠፈነበት አገር ወሣኝ በመሆኑ በቂ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሃገራት የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ጭምር ይሰጡታል፡፡ ከላይ ስለወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ከተሰጠው ፍቺም ለማረጋጥ እንደሚቻለው በሂደቱ ምንጊዜም ቢሆን የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እንዳለባቸው ነው፡፡ በመሆኑም የወንጀል ህግን ስራ ላይ ማዋል እና በወንጀል የተከሰሰን ሰው ሰብአዊ መብት ማክበር የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው፡፡

በሃገራችን ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያክል በሥራ ላይ የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተሸሮ በአዲስ የወንጀል ሕግ ተተክቷል፡፡ ነገር ግን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓቱ የተሻረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን በሥራ ላይ ለማዋል ወጥቶ በሥራ ላይ የነበረው አሁንም ድረስ ፀንቶ ያለ ሲሆን በቅርቡ ተሻሽሎ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህ ነባሩ ህግ ዝርዝር ጉዳዮችን የላካተተ በመሆኑ ለሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ከህጉ ምላሽ ማግኘት ከባድ ነው፡፡ ህጉ ሲሻሻል እነዚህ ክፍተቶች መሞላት አለባቸው፡፡ እስከዚያው ያለውን ህግ በአግባቡ ተርጉሞ ስራ ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡ ይኸው ህግ ያካታቸው በርካታ ጠቃሚ እና ዘመናዊ ድንጋጌዎች ለረዥም ጊዜ ባለመተግበራቸው የወንጀል ፍትህ ይጎተት እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ክፍተቶች ቢኖሩትም ያለውን ህግ እንዳለ ስራ ላይ የማዋሉ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተጨማሪ ግን ሌሎች የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ሕጎችን ያካተቱ ሕጎችም የሚገኙ ሲሆን ለአብነት ያክል የወነጀል ህጉ፣ አደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 384/96 እና የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥረዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከዚህ ሌላ ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድ ሦስተኛውን ቦታ የሚሰጠውና የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት መሰረታዊ ድንጋጌዎችን ያካተተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ እንደሌሎች ሃገሮች ሁሉ በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙና የታሰሩ ሰዎች ጉዳያቸው ሊስተናገድበት ስለሚገባበት ሁኔታ እና ስለ ሰብዓዊ መብታቸው አጠባበቅ ድንጋጌዎች ይገኛሉ፡፡ ዐ/ህግ እና ዳኞች ሁልጊዜ አግባብነት ያላቸውን የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተርጉመው ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ሲያደርጉ ግን በህገ መንግስቱ ለፌዴሬሽን ም/ቤት የተሰጠውን ስልጣን ማክበር አለባቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ህገ መንግሰቱ መተግበር አለበት፡፡ ለምሳሌ በህገ መንግሰቱ አንቀጽ 19/5 ስር በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም(inadmissible):: በተጨባጭ ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች አንጻር ታይቶ ማስረጃው በማስገደድ የተገኘ ነው ወይስ አይደለም? ተብሎ በዐ/ህግ ና ዳኞች መወሰን አለበት፡፡

በሕገ መንግሥቱ፣ በወንጀል ሕጉ ና በወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕጐቹ ተደንግገው የሚገኙት ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች ብቻ ሣይሆኑ የወንጀል ማስረጃን ጭምር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ማስረጃን በተመለከተ ሀገራችን የሲቪል ሎው የህግ ሥረዓትን ከሚከተሉት ሃገራት ተርታ ስለምትመደብ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን እንደሚከተሉ ሃገራት ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ የላትም፡፡ ከማስረጃ ጋር የተየያዙ ድንጋጌዎች በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተካተው ነው የሚገኙት፡፡

ለማጠቃለል ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሃገራችን ያሉት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ እነርሱም የሕገ መንግሥት መሠረት ያላቸው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ በሌሎች ሕጎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

# የመወያያ ነጥቦች

1. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ምንድነው ?
2. የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ና የአንድ ሃገር ሕገ መንግሥትን ምን ያገናኛቸዋል?
3. በሃገራችን የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ እናገኛቸዋለን?
4. የወንጀል ህግ ማስረጃስ በየትኞቹ ሕጎች ውስጥ ይገኛል?

5. ህገ መንግስታዊ መሰረት ያላቸውን የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ተርጉሞ ስራ ላይ በማዋል ረገድ ከዐ/ህግ እና ዳኞች ምን ይጠበቃል? በዚህ ረገድ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ህገ መንግስቱን ለመተርጎም ከተሰጠው ስልጣን ጋር እንዴት ያዩታል?

# ክፍል ሁለት

## የወንጀል ሥልጣን በፌዴራልና በክልል

### 2.1 የኢትዩÉያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያላቸው ስልጣን (Judicial Jurisdiction)አጠቃላይ

ፍርድ ቤቶች አንድ ክስ ከቀረበላቸው በኃላ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ማየትና ማራጋገጥ ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር ክሱን ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑ አለመሆኑን ነዉ። በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ ወደ ስረ ነገሩ መግባት የለባቸውም።

የፍ/ቤቶች ስልጣን ከኢትዮÉያ ሁኔታ ኣንፃር ሲታይ በአራት ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነዉ።

1. የኢትዮÉያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያለቸው ስልጣን
2. የክልል ወይም የፌዴራል ጉዳይ የማየት ስልጣን
3. በተለያየ ቦታ የሚገኙ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያላቸው ስልጣን
4. በወንጀሉ ዓይነት በሚደረገው ክፍፍል መሰረት ያላቸው ስልጣን ናቸው።

ከባህሪው ኣንፃር ሲታይ ደግሞ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ወንጀሎችን በሚመለከት ያላቸው ስልጣን ሁለት ባህሪያቶች ይዞ ይገኛል::

1ኛ. በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር ስላሉ ሰዎች ነው:: በኢዮጵያ የወንጀል ሕግ ስር ያሉ ሰዎች ሁሉ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር ናቸው:: በመሆኑም የወንጀል ሕግ ጥሰው ሲገኙ ፍርድ ቤት ቀርበው ይፈረድባቸዋል:: በወንጀል ሕግ ስር ስላሉና በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሰዎች ጉዳይ በወንጀል ሕግ አንደኛ መፅሓፍ ርእስ አንድ ምዕራፍ ሁለት ክፍል ሁለት (ከዓንቀፅ 11 እስከ 20) ተዘዝሮ ይገኛል::

2ኛ. ስለፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው:: የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይን ለማየት ያላቸው ስልጣንና ክሱም የት ቦታ መሰማት እንደሚገባው የሚመለከት ነው:: እነዚህ ጉዳዮች በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.4፣6፣7 እና ከ99-107 መሰረት የሚታዩ ናቸው::

## 2.2 በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስለሚዳኙ ሰዎች

አንድ ሰው በኤፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችሉት፣

ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ፣

ለ) የተከሳሹ ዜግነት፣ እና

ሐ) የተፈፀመው ወንጀል ዓይነት ናቸው፡፡

እነዚህ ነገሮች ደግሞ በኢትዩጵያ ዋና ስልጣን (Principal Jurisdication) ወይም ምትክ (አነስተኛ) (Subsidiary Jurisdication) ስር ሊወድቁ ይችላሉ :: ዋና እና ምትክ ስልጣን ብሎ የመለያየቱ አስፈላጊነት በስልጣኑ አፈፃፀም ልዩነት ስለሚፈጥር ነው:: ለምሳሌ:- አንድ በኢትዩጵያ ዋና ስልጣን ስር ያለ ሰው በውጭ አገር በወንጀል ተከስሶ ቢለቀቅ ወይም ነፃ ቢወጣ፣ ይህ ነፃ መውጣቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በዚያው ወንጀል ከመከሰስ አያድነውም:: ነገር ግን ሰውየው በኢትዮጵያ ምትክ (አነስተኛ) ስልጣን ስር ሆኖ እንዲህ ያለ ሁኔታ ቢደርስ ነፃ ይወጣል::

### 2.2.1 ዋና ስልጣን (Principal Jurisdiction) እና የዋናው ስልጣን ወሰን (የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 11-16)

#### 2.2.1.1 ዋና ስልጣን

ኢትዮጵያ በሚከተሉት ሰዎች ዋና ስልጣን አላት::

ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈፀመ ወንጀል የተከሰሰ ፣

ለ) በውጭ አገር ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ፣

ሐ) በውጭ አገር ወንጀል ሰርቷል ተብሎ በተከሰሰና ወንጀሉ በተሰራበት አገር ሰውየው የኢትዮጵያ መንግስት ሰራተኛ በመሆኑ የውጭ አገር የማይደፈር መብት ያለው ሲሆን ፣ እና

መ) በውጭ አገር ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ በተከሰሰ የኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት አባል ነው፡፡

**ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚሰሩ ወንጀሎች (ዓንቀፅ 11-12)፡**

ዓንቀፅ 11(1) በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በወንጀል ሕግ ከተጠቀሱት ማንኛውንም ወንጀል የሰራ ማነኛውም ሰው በዚሁ ሕግ መሰረት እንደሚቀጣ ይገልፃል:: (ግዛት ሲባል የብስና አየርም ይጨምራል)፡፡

<u>ለምሳሌ</u>:- አንድ የግብፅ ዜጋ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 620 በመተላለፍ በሌላ ግብፃዊት ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈፅሞባታል ቢባል ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በመሆኑ ተከሳሹ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር ነው:: ስለዚህ የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 620 ጥሰሃል ተብሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል::

<u>ለምሳሌ:</u>- አንድ የኬንያ አየር መንገድ ኤሮፕላን በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ሲበርር ኤሮፕላኑ ውስጥ አንዱ የኬንያ ዜጋ ሌላውን የኬንያ ዜጋ ቢደበድበው ወንጀሉ የተፈፀመው ኢትዮጵያ አየር ላይ በመሆኑ (አየሩ የኢትዮጵያ ግዛት ነው) ወንጀሉ የተሰራው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ነው:: ይህም ደብዳቢውን በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር ያደርገዋል :: ስለዚህም ዓንቀፅ 560 ተላልፈሃል ተብሎ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል::

በዓንቀፅ 11(3) እንደተመለከተው አንድ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል ሰርቶ ከኢትዮጵያ አምልጦ በሌላ አገር ጥገኝነት ጠይቆ ቢቀመጥ የኢትዮጵያ መንግስት ወንጀለኛውን በጥገኝነት ያስቀመጠው መንግስት አሳልፎ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል:: የኢትዮጵያ መንግስት ይህ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግን የዚህ ዓይነት ስምምነት ጥገኝነትን ከሰጠች አገር ጋር ያለው እንደሆነ ነው:: ስምምነት ከሌለ ጥገኝነት በሰጠች አገር እንዲከሰስና እንዲፈረድበት ኢትዮጵያ መጠየቅ ትችላለች::

በዛው አገር ተከስሶ ነፃ የተባለ እንደሆነ በውጭ አገር ተፈርዶበት ምሕረት ወይም ይቅርታ ተደርጎለት እንደሆነ ወይም ክሱ ወይም ቅጣቱ በይርጋ ምክንያት ተሰርዞለት እንደሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ቢያዝም ሊከሰስና ሊቀጣ አይቻልም (ዓንቀፅ 12(2)::

ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት ተጠርጣሪው ጥገኝነት በጠየቀበት አገር ውስጥ እንዲከሰስ አስጠጊውን አገር ባይጠይቅና አስጠጊው መንግስት ራሱ ከስሶ በነፃ ቢለቀውና በኃላ ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ እንደገና በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል:: (ዓንቀፅ 16(2))::

ሌላው በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ ሳይፈፅም ወይም በከፊል ብቻ ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ ቢገባ ያልተፈፀመው ቅጣት በኢትዮጵያ ይፈፀማል (ዓንቀፅ 12(3)):: ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ግን በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ነው::

**ለ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች (ዓንቀፅ 13)፡**

ይህ ዓንቀፅ የሚመለከተው በኢትዮጵያ መንግስት በደህንነቱ ወይም አንድነቱ ላይ በሕጋዊ ተቋማቱ ወይም ዋና ዋና ጥቅሞቹ ወይም በገንዘቡ ላይ ወንጀል ባደረገ በማናቸውም ሰው ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ነው:: እነዚህ ወንጀሎች በወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 238 - 260 እና 355 - 374 ስር የሚወድቁ ናቸው::

ለምሳሌ:- አንድ የውጭ አገር ዜጋ በውጭ አገር ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን የኢትዮጵያ መንግስትን ለመገልበጥ ውጭ አገር ሆኖ ቢያድምና ይህንኑ አድማ ለማከናወን የሐሰት ገንዘብ (በኢትዮጵያ ገንዘብ መልክ) ቢያሳትም ወንጀሉ ዓንቀፅ 238 እና 357 ስለሚጥስ በዓንቀፅ 13 መሰረት በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ነው::

**ሐ) የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ መንግስት የመከለከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር ሆኖው የሚያደርጉዋቸው ወንጀሎች (ዓንቀፅ 14 እና 15)፡**

በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖች ሁሉ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ናቸው:: በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት መከላከያ ሰራዊት አባላትም እንደዚሁ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሲሆኑ ነገር ግን እንደ ወንጀሉ ዓይነት አንዳንድ ጊዜ በዋና ስልጣን ሌላ ጊዜ ደግሞ በምትክ (አነስተኛ) ስልጣን ስር የሚወድቅበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል::

ሌሎች በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ደግሞ በዓንቀፅ 13 የተጠቀሱትን ወንጀሎች ካልፈፀሙ በስተቀር በኢትዮጵያ ምትክ ስለጣን ስር ናቸው (ዓንቀፅ 18)::

የማይደፈር መብት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን በውጭ አገር በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሊወድቁ የሚችሉ (በዓንቀፅ 13 ከተመለከተው ውጭ) በኢትዮጵያ እና ወንጀል በተፈፀመበት አገር ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ነው::

የመከላከያ ሰራዊት አባል በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 269 እስከ 322 የተጠቀሱትን ወንጀሎች በመስራት የዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም ወታደራዊ ጠባይ ያለውን ወንጀል የሰራ እንደሆ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሆኖ በጦር ፍርድ ቤት ላይ ይከሰላል:: ከዓንቀፅ 269 እስከ 322 ውጭ የሆኑትን ድንጋጌዎች ቢጥስ ግን በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው የሚሆነው::

## 2.2.1.2 የዋናው ስልጣን ወሰን (የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 16)

ኣንድ ሰው በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሲሆን ተሰርቷል የተባለው ወንጀል በጣም የሚጎዳው ወይም የሚነካው የኢትዮጵያ ግዛት ነው ማለ ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ምትክ ስልጣን ወሰን ኣይመለከተውም::

በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ያለ ሰው በሰራው ወንጀል በውጭ ኣገር ቢከሰስም ባይከሰስም በክሱም ነፃ ቢወጣ ወይም ባይወጣ ወይም ቢፈረድበት ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ወይም የውጪው ኣገር ኣሳልፎ ሲሰጠው ኢትዮጵያ ውስጥ ለፍርድ ይቀርባል::
በዋናው ስልጣን ላይ ያለው ወሰን ወንጀለኛው በውጭ ኣገር ተፈርዶበት የተቀጣው ቅጣት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚወሰንበት ቅጣት ላይ የሚቀነስበት መሆኑ ብቻ ነው::

ሆኖም ወንጀሉን የፈፀመው ሰው በውጭ አገር ፍርድ ቤት ተከሶ የተፈረደበት በኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ መሰረት ከሆነ (የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 12) ወንጀለኛው በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር እንደማይሆንና ኢትዮጵያን የማይደፍር መብት ባላቸው የዲፕሎማቲክ መልእክተኞች ላይ ያላትን ስልጣን ዓንቀፅ 14 በመጠኑ እንደሚወሰነው ማየት ይቻላል፡፡

## 2.2.2 ምትክ / አነስተኛ/ ስልጣን (Subsidiary Jurisdiction)

የኣነስተኛ ስልጣን ፍቺው ተሰራ የተባለው ወንጀል ኢትዮጵያን በጣም የማይነካ ወይም የማይጎዳ ሲሆን ነው፡፡ የሚከተሉትን ወንጀሎች የፈፀሙ ተከሳሾች በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ናቸው፡፡

ሀ) በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥስ ወይም የህዝብን ጤንነትና ሞራል የሚጎዳ ወንጀል ሰርቷል በመባል የተከሰሱ፣

ለ) ለውጭ አገር አንዳንድ ወንጀሎችን በኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ፈፅመዋል በመባል የተከሰሱ እና

ሐ) በውጭ አገር በማንኛውም ሰው ላይ ከባድ ወንጀል ፈፅመዋል በመባል የተከሰሱ ኢትዮጵያዊያንና በውጭ አገር የአገሩን ተራ ሕግ በመጣስ ወንጀል ሰርተው አምልጠው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ወታደሮች ናቸው፡፡

**ሀ) በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ስላሉ ሰዎች፣**

1. በዓለም አቀፍ ሕግና ስርዓት ላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ወንጀሎች (ዓንቀፅ 17)&

በዓንቀፅ 14 እና 15(2) ከተደነገጉት (ዓንቀፅ 17(2)) ወንጀሎች ውጭ በዓንቀፅ 17 የተጠቀሱትን ወንጀሎች የፈፀመ ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው፡፡

በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው ተብሎ የተደነገገውን ወንጀል የፈፀመ ወይም ኢትዮጵያ በተስማማችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት ወንጀል ነው ተብሎ የተወሰነውን የፈፀመ ማነኛውም ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው፡፡ ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ከዓንቀፅ 269 እስከ 283 የተዘረዘሩትን ሲሆኑ ፣ ሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱት ወንጀሎች ደግሞ በነጋሪት ጋዜጣና ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ወንጀል ጠቀስ በሆኑ ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የህዝብን ጤንነት ወይም ሞራል የሚጎዱ ወንጀሎችን በውጭ አገር የፈፀሙ ሰዎች በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ናቸው፡፡ እነዚህም ወንጀሎች በዓንቀፅ 525 (መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሓኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም)፣ በዓንቀፅ 599 እና 636 እስከ 641 የተመለከቱትን ናቸው፡፡

2. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ሌሎች ወንጀሎች (ዓንቀፅ 18)

ሀ) በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር የሚሆነው፣ ያደረገው ጥፋት በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወይም ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከኢትዮጵያ ውጭ በላይ በተመለከቱት (ዓንቀፅ 11-17) ከተገለፁት ወንጀሎች ሌላ የፈፀመ እንደሆነ፣ አድራጊው በዚሁ ወንጀል በውጭ አገር ሳይከሰስ ከቀረ ይህ የወንጀል ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል:: ይህ ለማድረግ ግን:-

1) ድርጊቱ በተፈፀመበት አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጎ እንደሆነ፣ እና
2) የተፈፀመው ወንጀል ከባድ በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ተከሳሹ ተይዞ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማድረግ በቂ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ነው::

<u>ለምሳሌ</u>:- "ሀ" እና "ለ" የተባሉ ሁለት አገሮች አሉ እንበል:: ከ "ለ"ጋር ኢትዮጵያ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል የፈፀመ ሰው አሳልፎ ይሰጣል የሚል ስምምነት አላት:: ከ "ሀ" ጋር ግን ይህ ስምምነት የላትም ::: በዚህ መሰረት አንድ የ "ለ" አገር ተወላጅ በ "ሀ" አገር አንዱን ኢትዮጵያዊ ቢገድለው ይህም በ "ሀ" አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ (ዓንቀፅ 540) ወንጀል ስለሆነ ገዳዩ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ይሆናል:: ምክንያቱም፤

1) ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ በመሆኑ ፤
2) ወንጀሉ በኢትዮጵያም በ "ሀ" ም አገር ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ በመሆኑ ፤ እና
3) ወንጀሉ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት አሳልፎ ለመስጠት በቂ ከባድነት ያለው በመሆኑ ነው::

ለ) ማንም የውጭ አገር ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ በዚህ ሕግ ተላልፎ ካልተሰጠ ወይም በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰስ የሚችለው (በኢትዮጵያ አነስተኛ ስልጣን ስር የሚሆነው) የሰራው ወንጀል ከአስር ዓመት ባለነሰ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ነው (ዓንቀፅ 18(2))::

ዓንቀንፅ 18(2) ከንኡስ ቁጥር (1) የሚለየው:- ንኡስ ቁጥር (2) የሚያመለክተው፤ አንደኛ፡ ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ዜጋ ላይሆን ይችላል፤ ሁለተኛ፡ የተሰራው ወንጀል ከአስር ዓመት ፅኑ እስራት ባላነሰ ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል መሆን አለበት::

3. ኢትዮጵያ ውጭ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል ስለሚሰራው ወንጀል (ዓንቀፅ 15(1)::

ማንም የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር መደበኛ ሕግን ቢጥስ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ይሆናል:: ወንጀል በፈፀመበት አገር ሊከሰስና ሊፈረድበት ይቻላል:: ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ እንደሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ይዳኛል (ዓንቀፅ 21(2))::

**ለ) የምትክ ስልጣን ወሰን (ዓንቀፅ 19(4) እና 20)**

በዓንቀፅ 19(4) እንደተመለከተው አንድ ሰው በውጭ አገር ወንጀል ሰርቶ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ቢሆን የውጭ አገሩና የኢትዮጵያ የወንጀል ሕጎች በሚደነግጉት ቅጣት መካከል ልዩነት ያለ እነደሆነ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሹን የሚጠቅመው መሰረት በማድረግ ይሆናል::

ለምሳሌ:- ወንጀሉ በተሰራበት አገር በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ በኢትዮጵያ ሕግ ግን በሞት የሚያስቀጣ ቢሆን የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተፈፃሚ የሚያደርጉት የዕድሜ ልክ እስራትን የሚያዘው ሕግ ይሆናል ማለት ነው::

አንድ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር የሚወድቅ ሰው በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ ከወጣ ወይም አያስከስሰውም ከተባለ እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማይከሰስ ከሕጉ መገንዘብ ይቻላል (ዓንቀፅ 20(1))::

ለምሳሌ:- በአንድ አገር ውጊያ ተደርጎ አንድ የአገሩ ተወላጅና አንድ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል በውጊያው ጊዜ የሰው ሃብት ቢዘርፉና በዚያው አገር ሕግ ተከሰው ነፃ ከወጡ በኃላ ወደ ኢትዮጵያ ቢገቡ፣ የውጭው አገር ተወላጅ በዓንቀፅ 17(1) መሰረት በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ሲሆን ኢትዮጵያዊው የመከላከያ ሰራዊት አባል ግን በዓንቀፅ 15(2) መሰረት በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ነው:: በዚህ ሁኔታ የውጭው አገር ተወላጅ ወታደር በኢትዮጵያ እንደገና አይከሰስም፤ ኢትዮጵያዊው ግን የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 273 በመተላለፉ እንደገና ሊከሰስና ሊቀጣ ይቻላል::

**ሐ) ምትክ ስልጣንን ስለሚጠቅሱ ሌሎች ጉዳዮች / ዓንቀፅ 19(1) እና (2) / ፤**

በዓንቀፅ 19(1) መሰረት በኢትዮጵያ ወይም ወንጀሉ በተፈፀመበት አገር ሕግ ወንጀል ሰሪው ተከስሶ እንዲፈረድበት፣

1. ወንጀሉ የሚያስከስሰው በግል አቤቱታ ብቻ ሲሆንና አቤቱታው ቀርቦ እንደሆነ፣
2. አድራጊው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተገኘ እንደሆነና ተላልፎ ያልተሰጠ እንደሆነ፣ ወይም ለኢትዮጵያ ተላልፎ ተሰጥቶ እንደሆነ፣ ወይም
3. ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን በፈፀመበት አገር ይቅርታ ያላገኘ እንደሆነ ወይም ወንጀሉ በተደረገበት አገር ሕግ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ በይርጋ ያልታገደ እንደሆነ ነው፡፡ ሆኖም ዓ/ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት የፍትሕ ሚኒስትሩን ማማከር እንዳለበት ተመለክቷል /ዓንቀፅ 19/3//፡፡

## 2.2.3 የዋና እና የምትክ ስልጣን ማጠቃለያ

### 2.2.3.1 ዋና ስልጣን

ሀ) የሚከተሉት ሰዎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዋና ስልጣን ስር ናቸው፡፡

1. በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወንጀል የሰሩ ሰዎች (ዓንቀፅ-11)
2. በውጭ አገር ከዓንቀፅ 238-260 እና 355-374 የተከለከሉትን ወንጀሎች በኢትዮጵያ ላይ የሰሩ ሰዎች (ዓንቀፅ 13)
3. ብውጭ አገር በአገሩ ሕግና በኢትዮጵያ ሕግ የተከለከለ ወንጀል የሰሩ በውጭ አገር የማይደፈር መብት ያላቸው የኢትዮጵያ መልእክተኞች (ዓንቀፅ 14)
4. ዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ ወይም በዓንቀፅ 269-322 የተመለከቱትን ወታደራዊ ሕግ በመጣስ በውጭ ኣገር ወንጀል የሰሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት (ዓንቀፅ 15)

ለ) የሚከተሉት ዋናውን ስልጣን የሚመለከቱ መሰረተ ሓሳቦች ናቸው፡፡

1. ኣንድ ወንጀለኛ በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ መውጣቱ ኣጥፊው የተከሰሰው በዓንቀፅ 12 መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ ኣቅርቦ ካልሆነ በስተቀር ወንጀለኛውን እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ ከመከሰስ ኣያድነውም (ዓንቀፅ 16(1) (2))

2. ወንጀሉን በሰራበት አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ በከፊል ወይም በሙሉ የተፈፀመበት ተከሳሽ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈረደበት ቅጣት ላይ በውጭ አገር የተፈፀመበት ቅጣት ይቀነስለታል (ዓንቀፅ 16(3))

### 2.2.3.2 ምትክ ስልጣን

ሀ) የሚከተሉት ሰዎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር ናቸው፡፡

1. በውጭ አገር የአገሩን ተራ ሕግ በመጣስ ወንጀል ሰርተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት (ዓንቀፅ 15(1))
2. በውጭ ኣገር ዓለም ኣቀፍ ሕግን በመጣስ (ዓንቀፅ 269 እስከ 286) ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ስምምነት ዓለም ዓቀፍ ወንጀል የተባሉትን በመጣስ ወይም ዓንቀፅ 525፣599፣637፣640 እና 641 በመጣስ ወንጀል የሰራ ማንኛውም ሰው (ዓንቀፅ 17)

3. በውጭ ኣገር በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወንጀል የሰራ ማነኛውም ዜጋ ወይም በውጭ አገር ወንጀል የሰራ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር የማይሆን ኢትዮጵያዊ፤ይኸውም የሚሆነው (1ኛ) ጥፋቱ በኢትዮጵያም

በውጭው አገር ሕግም ወንጀል ሆኖ ሲቆጠርና (2ኛ) ወንጀሉ በኢትዮጵያ ሕግ ወንጀለኛውን ኣሳልፎ የሚያሰጥ ሲሆን ነው (ዓንቀፅ 18(2))

ለ) የሚከተሉት አነስተኛ ስልጣንን የሚመለከቱ መሰረተ ሓሳቦች ናቸው፡፡

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በኣጥፊው ላይ የሚፈረደው ቅጣት ወንጀሉ በፈፀመበት አገር ሕግ ለወንጀሉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት ኣይበልጥም (ዓንቀፅ 19(4))
2. ወንጀለኛው በውጭ ኣገር ተከስሶ ነፃ የወጣ ወይም ከክሱ የተሰናበተ እንደሆነ እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ ኣይከሰስም (ዓንቀፅ 20(1))
3. በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ በከፊል የተፈፀመበት ወንጀለኛ ቅጣቱ በይርጋ ካልታገደ በስተቀር ቀሪው ቅጣት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀምበት ሊፈረድበት ይችላል (ዓንቀፅ 20(2))

# ክፍል ሦሥት

## የክልል ወይም የፌዴራል ጉዳይን የማየት ስልጣን

የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግስት የዳኝነት አካል በፌዴራልና በክልል ደረጃ እንደሚዋቀሩና የየራሳቸው የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ይገልፃል፡፡ የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን በየክልሉ ብቻ የተወሰነ ሲሆን የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ግን በአ/አበባና ድሬዳዋ ብቻ የታጠረ ሳይሆን ብጉዳዩች ዓይነት ተለይቶ ወደ ሁሉም ክልሎች ሊደርስ ይችላል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ኣዋጅ ቁጥር 25/88 በዓንቀፅ 4 ላይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ያላቸውን ስልጣን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚሀ ዓንቀፅ ላይ የተዘረዘሩት ወንጀሎች በየተኛውም ክልል ተፈፅመው ሲገኙ ጉዳዩቹን ኣይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆኖው በክልሎች ውስጥ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች የክልል ፍ/ቤቶች በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 78 (2) ባገኙት ውክልና መሰረት ከራሳቸው ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሆነውን የወንጀል ጉዳይም ደርበው ያየሉ፡፡

የፌዴራል ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉደዮች ላይ ያላቸው ስልጣን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

1. በሕገ መንግስታዊ ስርዓቱና በመንግስት የሃገር ዉስጥ ፀጥታ ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች የወ/ሕግ ዓንቀፅ 238-260 ፣
2. በውጭ አገር መንግስት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 261-268) ፣
3. በሰው ልጆች መብት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 269-283) ፣
4. በፌዴራል መንግስቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
5. የሐሰት ገንዘብን በሚመለከቱ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 356-362) ፣
6. በፌዴራል መንግስት ሰነዶች ላይ የሐሰት ስራ በመስራት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣

7. ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነፃነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
8. የበረራ ደህንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች ፣
9. የውጭ አገር ዜጎችን በሚመለከቱ ወንጀሎች ፣
10. የአደገኛና አደንዛዥ ዕፆች ሕገ ወጥ ዝውውርን በሚመለቱ ወንጀሎች ፣
11. በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌዴራልና በክልል ፍ/ቤቶች የስልጣን ክልል ስር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች ፣ እና
12. የፌዴራል መንግስቱ ባለስልጣኖችና ሰራተኞች በስራቸው ወይም በሃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከእነዚህ መካከል በተራ ቁጥር 1 - 3 ፣ 5 ፣ እና ከ7 - 11 የተጠቀሱትን የወንጀል ጉዳዮች የፌዴራል ፍ/ቤቶች ብቻ የሚያዩዋቸው (Exclusive Jurisdiction) ሲሆኑ ሌሎች በተራ ቁጥር 4 ፣ 6 እና 12 የተመለከቱትን ጉዳዮች ግን ክልሎችም ከክልላቸው ጋር የተያያዘ በሚሆንበት ጊዜ የክልል ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ ክልሎች በፍ/ቤት ማማቋቋሚያ አዋጆቻቸው ላይም ደንግገውት ይገኛል፡፡

ከዚህ ጋር ተያያዞ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ የወንጀል ሕግ የማውጣት ስልጣን የፌዴራል የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት መሆኑን ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 55(5) መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክልል ምክርቤቶች ወንጀልን በተመለከተ ሕግ የማውጣት ስልጣን የሚኖራቸው በፌዴራሉ መንግስት የወንጀል ሕግ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ ግን የወንጀል ሕጉ በፌዴራል መንግስት ቢወጣም ክልሎች በራሳቸው ምክርቤቶች እንደወጡ ሕጎች ዓይነት በፌዴራሉ የወንጀል ሕግ ላይም የዳኝነት ስልጣን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

# ክፍል አራት

# የሥረ ነገርና ክልላዊ ሥልጣን

## 4.1 የስረ ነገረ ስልጣን /Material Jurisdiction/

የስረ ነገር ስልጣን ሲባል አንድ የወንጀል ዓይነት የሚመለከት ክስ በየተኛው ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት የሚወስን ስልጣን ነው፡፡ ይህ ማለትም ጉዳዩ መታየት ያለበት በወረዳ /በመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፣ በዞን /ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ወይስ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው የሚል ጥያቄ የሚመልስልን ነው፡፡

ለምሳሌ፡ የክልል ፍርድቤቶች ስልጣን በወረዳ፣ በዞንና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተከፋፈለ ነው፡፡ አንዳንድ ክልሎች ቀላል የወንጀል ጉዳዮችን በማህበራዊ ፍርድ ቤት እንዲዳኙ ስልጣን የሰጡበት ሁኔታም አለ /የትግራይ ክልልን መጥቀስ ይቻላል/፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶችም በመጀመሪያ ደረጃ፣ በከፍተኛ እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶች በማቋቋሚያ አዋጃቸውን ለይተው አስቀምጠዋል፡፡

የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 4 ፍርድ ቤቶች የሚያዩዋቸውና የሚፈርዱባቸው በዚሁ የስነ ስርዓት ሕግ በአንደኛው ሰንጠረዥ መሰረት እንደሆነ ያዝዛል፡፡ ይህ ሰንጠረዥ ግን ሕጉ ሲወጣ በነበረው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር መሰረተ የተዘጋጀ መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡ የደርግ መንግስት ከተገረሰሰ በኃላ ግን የፍርድ ቤቶች ስልጣን በሚመለከት አንዳንድ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ለውጦች አንዱ ደግሞ ድሮ በአውራጃ ይታየ የነበረ የወንጀል ዓይነት በአሁኑ ጊዜ አውራጃ የሚባል ነገር ስለሌለ ለወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ወንጀሎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡

የተሰራው ወንጀል በወንጀል ሕግ የሌለ ቢሆን፣ እንበል አንድ ሰው በሌላ አዋጅ የወጣ ድንጋጌ ቢጥስ የተኛው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንዳለው የሚወስነው ለጥፋቱ የተመደበውን ከፍተኛ የቅጣት ወሰን በመመልከት ነው፡፡ አሁን ያለው የፍርድ ቤት አወቃቀር መሰረት አድርግን ስናየው ከፍተኛው ቅጣት ከአምስት ዓመት እስራት የማይበልጥ ከገንዘብ መቀጮ ጋር ወይም ያለመቀጮ ቢሆን፣ በጉዳዩ ላይ ስልጣን የሚኖሮው ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ከፍተኛው ቅጣት ከአምስት ዓመት እስራት በላይ ከሆነ ግን ጉዳዩ የሚሰማው በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ በስነ ስርዓ ሕጉ አንደኛ ሰንጠረዥ መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ለማየት ያላቸው ስልጣን በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.182 መሰረት እንደሆነ የስነ ስረዓቱ ቁ.7 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም አዲስ የመንግስት አወቃቀር ከተደረገ በኃላ በዚህ ዙሪያ ለውጦች ተደርገዋል፡፡

<u>ለምሳሌ፡</u> የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.25/88 ያየን እንደሆነ አንድ የወንጀል ጉደዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ከተወሰነ ወደሚቀጥለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት እንደሚቻልና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያው ፍርድ ቤት ውሳኔ ያፀናው እንደሆነ ሁለተኛ ይግባኝ ማለት እንደማይፈቀድ ያመለክታል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች ለምሳሌ ትግራይ ክልል በወራዳ ፍርድ ቤት የተወሰነ ጉዳይ ለዞን ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቢፀናም ቢሻርም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት እንደሚቻል ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ አሁንም ቢሆን_እየተሰራ ያለው የወ/መ/ሕ/ስ/ስ ባስቀመጠው ስልጣን መሰረት በመሆኑ ነው፡፡

### 4.2 <u>ክልላዊ ስልጣን (Local Jurisdiction)</u>

ይህ ዓይነት ስልጣን የት ወረዳ ወይ ዞን ያለ ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የሚለውን ነገር በማየት የሚወሰን ነው፡፡ እንደ ወንጀሉ ዓይነት ክሱ መታየት ያለበት በወረዳ ፍርድ ቤት የሆነ እንደሆነ በየተኛው ኣከባቢ ያለ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው ክሱ መታየት ያለበት የሚለውን ነገር የሚወስን

ነው፡፡ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 6 እንደሚያመላክተው በተለያዩ አከባቢ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 99-107 የተወሰነላቸው ቦታ መሰረት አድርገው የዳኝነት ተግባራቸውን የማከናወን ስልጣን እንዳላቸው ነው፡፡

ማንኛውም የወንጀል ክስ ወንጀሉ በተፈፀመበት አከባቢ በሚገኘው ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የወ/ወ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.99 ይደነግጋል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- የወንጀሉ ዓይነት በወረዳ ፍ/ቤት የሚታይ ሊሆን ይችላል፡፡ የወረዳ ፍ/ቤት ስልጣን ነው ማለት ግን የትም አከባቢ የሚገኝ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ማለት እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ወረዳ ፍ/ቤት ነው የሚለውን ብቻ ሳይሆን የት አከባቢ ያለ የወረዳ ፍ/ቤት ነው የሚለውን ጥያቄም አብሮ ሊመለስ የሚገባው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀሉ የተፈፀመበትና የወንጀሉ ወጤት የታየበት አከባቢ የተለያየ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህም ማለት ወንጀሉ የተፈፀመው በአንድ ወረዳ ወይም ዞን ሲሆን የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ወረዳ ወይም ዞን ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ሁለቱ ፍ/ቤቶች ማለትም ወንጀሉ በተፈፀመበት አከባቢ የሚገኝ የወረዳ ወይም የዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት ወይም የወንጀሉ ውጤት በታየበት አከባቢ የሚገኝ የወረዳ /ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የክልል ስልጣን (Local Jurisdiction) አላቸው ማለት ነው፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን ወንጀሉ የተፈፀመው በአንድ የክልል መስተዳደር፣ የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ክልል መስተዳደር የሆነ እንደሆነም በአንዳቸው ክልል መስተዳደር ስር የሚገኝ የስረ ነገር ስልጣን ያለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን ነው፡፡

<u>ለምሳሌ፡-</u> አንድ የምስራቅ ሸዋ ዞን ሰው በአዳማ ከተማ ሰውን ለመግደል አስቦ የተመረዘ ሰርዲን (የታሸገ የዓሳ ስጋ) ቢልክለትና ግለሰቡ በዚሁ ምክንያት ቢሞት ጉዳዩ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም በአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊሰማ ይችላል፡፡

አንዳንድ ተግባሮች ደግሞ ከወንጀል ስራዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ወንጀል ይሆናሉ፡፡

<u>ለምሳሌ፡</u> አንዱን ሰው በሐሰት እንዲመሰክር መገፋፋት የማታለል (ማጭበርበር) ወንጀል እንዲሰራ ስለሚያደርግ እንዲህ ያለው ተግባር በወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 455 መሰረት የተከለከለና የሚያስቀጣ ነው፡፡ በሐሰት እንዲመሰክር የመገፋፋት ተግባር ራሱ ወንጀል ሲሆን ይህ ወንጀል ከሁለቱ አንዱ ወንጀል በተፈፀመበት ስፍራ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሊሰማ እንደሚችል ይደነገግጋል (የወ/መ/ሕ/ሰ/ሰ/ቁ.101)

<u>ለምሳሌ</u>፡- በሰሜን ሸዋ ዞን አንድ ሰው ሌላውን፣ በደቡብ ወሎ ዞን በሚታይ ክስ በሐሰት እንዲመሰክር ያደርገዋል፡፡ ይህ ወንጀል ዓንቀፅ 455ን በመጣሱ በዞን ፍ/ቤት መታየት የሚገባው በመሆኑና የወንጀል ስራው የተሰራ በሰሜን ሸዋ ዞን ሲሆን ከስራው ጋር ግንኙነት ኖሮት ወይም በስራው ምክንያት የተፈፀመው ወንጀል የተሰራው በደቡብ ወሎ ዞን በመሆኑ አጥፊው በሰሜን ሸዋ ዞን ፍ/ቤት ወይም በደቡብ ወሎ ዞንፍ/ቤት ሊከሰስ ይችላል፡፡

ቀጥሎ የሚነሳ ጉዳይ ደግሞ ወንጀሉ የት እነደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆንስ ክስ መሰማት ያለበት የት ነው የሚለውን ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102(ሀ) ያሰቀመጠው መፍትሄ አለ፡፡ በአንቀፁ እንደተመለከተው ወንጀሉ የት እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን ክሱ ስልጣን ባለው በአንድ ስፍራ በሚገኝ ፍርድ ቤት ሊሰማ እንደሚቻል ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው የወንጀል ሕግ ዓነቀፅ 665ን በመተላለፍ አንድ በሬ ቢሰርቅ ወንጀሉ መሰማት የሚገባው በወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ከየት እንደሰረቀው ለይቶ ባያውቅና ከዳንሻ ወረዳ ወይም ከፀገዴ ወረዳ ከሁለቱ አንዱ መሆኑ ግን ግልፅ ቢሆን ተጠርጣሪው በዳንሻ ወይም በፀገዴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊከሰስ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀሉ በከፊል ግማሹ በአንድ ስፍራ ግማሹ ደግሞ በሌላ ስፍራ ሲፈፀም (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102(ለ) ወይም ወንጀሉ በብዙ ስፍራዎች ያለማቋረጥ ሲፈፀም (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.102(ሐ) ወይም ወንጀሉ በልዩ ልዩ ቦታዎች በተሰሩ ልዩልዩ ተግባሮች የተፈፀመ ሲሆን (ቁ.102(መ)) ክሱ በአከባቢው ካሉት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማንኛውም ሊሰማ ይችላል፡፡

ምሳሌ 1፡- በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች ብንወስድ አንዱ ሰው ሌላውን መጀመርያ በደቡብ ዞን ውስጥ (ወሰን አከባቢ) በጩቤ ወግቶ ጥሎ ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ ጎትቶ በመውሰድ እንደገና በጩቤ ወግቶ የግድያ ሙከራ ቢፈፅምበት ወንጀሉ በከፊል ደቡብ ዞን በከፊል ደግሞ ደቡብ ምስራቅ ዞን ውስጥ ስለተፈፀመ በደቡብ ወይም በደቡብ ምስራቅ ዞን በሚገኝ የዞን ፍ/ቤት ሊሰማ ይችላል፡፡

ምሳሌ 2፡- ተከሳሹ ያለአግባብ አንዱን ሰው በአላማጣ ወረዳ ቢይዘውና መሆኒ ወረዳ ወደ ሚገኘው ፓሊስ ጣቢያ ቢወስደው የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 584 በመጣስ ወንጀል ስለሚሰራና የወንጀሉ ስራ ሰውየውን ያለ ሕግ በግድ መያዙ ያለማቋረጥ ስለቀጠለ ክሱ በአላማጣ ወይም በመሆኒ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊታይ ይቻላል፡፡

ምሳሌ 3፡- ተከሳሹ በምስራቅ ሸዋ ዞን ሆኖ በምዕራብ ሸዋ ዞን ላለ ሰው የያዘው ግመል የእርሱ መሆኑን በመግለፅ የሐሰት ደብዳቤ ይፅፍለታል፡፡ ቀጥሎም ወደ ምዕራብ ሸዋ ዞን ሄዶ በማታለል ግመሉን ይረከባል፡፡ የሰራውም ወንጀል የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 692 ይጥሳል፡፡ ወንጀሉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛው የሐሰት ደብዳቤ መፃፉ ሁለተኛው ደግም ግመሉን በዚሁ በማጭበርበሪያ ደብዳቤ መሰረት መረከቡ ናቸው፡፡ ደብዳቤው የተፃፈው በምስራቅ ሸዋ ዞን ስለሆነ ክሱ በምስራቅ ሸዋ ወይም በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሰማ ይቻላል፡፡

በቁ.103 መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ቢሆን ተጠርጣሪው ወይም ወንጀሉ ተየፈፀመበት ሰው ወይም ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ስፍራ ውስጥ ክሱን ለመስማት ስልጣን ባለው ፍርድ

ቤት ክሱ ይታያል፡፡ ተጠርጣሪው ወንጀል የፈፀመበት ሰው ወይም ሌላ ነገር (ንብረት) በስፍራው ካለፈ ወንጀሉ በዛው ስፍራ ባይፈፀምም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በነገሩ ሊፈርድ እንደሚችል ነው፡፡

ምሳሌ 1፡- በአንድ ከየካ ክፍለ ከተማ ባአራዳና በአዲስ ክፍለ ከተማ አድርጎ ወደ ኮላፌ ቀራንዩ በሚሄድ አውቶብስ ውስጥ አንድ ሰው በየካ ተሳፍሮ ሌላውን መንገደኛ ተሳፍሮ ደብድቦ በዚያው በየካ ክፍለ ከተማ ቢወርድና ተበዳዩ (ተደብዳቢው) ደግሞ አራዳ ክፍለ ከተማ ቢወርድ ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው በጉዞው ጊዜ በአራዳ ክፍለ ከተማ ስላለ አጥፊው የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 582 ተላልፎ በሰራው ወንጀል በየካ ወይም በአራዳ ምድብ ችሎት ሊከሰስ ይችላል፡፡

ምሳሌ 2፡- በኮምቦልቻ ወረዳ በመኪና የተጫነ የንግድ እቃ በደብረሲና አቋርጦ ደብረብርሃን ሲደርስ ቢሰረቅ እቃው በሶስቱም ወረዳዎች ውስጥ ስላለፈ ወንጀለኛው ከሶስቱ ወረዳ ፍርድ ቤቶች በማንኛውም ሊከሰስ ይችላል፡፡

አንድ ወንጀል ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በኢትዩጵያ መርከብ ላይ ወይም ኤሮፕላን ውስጥ ቢፈፀም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈፀመ ይቆጠራል ይላል (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.104)፡፡ ይህ ቁጥር ክሱ በየትኛው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው አይገልፅም፡፡ ሆኖም ቁ.107 ከቁ.100 እስከ 104 የተመለከቱትን ዓይነት ወንጀሎች ሁሉ ክሱ በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት ዓቃቤ ሕጉ ሊወስን እንደሚችልና ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንደሚኖረው ይገልፃል፡፡ ስለዚህ አንድ ክስ በብዙ ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል ሲሆን በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ዓቃቢ ሕጉ ይወስናል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኤሮፕላን በሱዳን ላይ ሲበርና በወረዳ ፍርድ ቤት መታየት የሚገባው ወንጀል በኤሮፕላኑ ውስጥ ቢፈፀም ጉዳዩ ዓቃቤ ሕግ በሚመርጠው በማንኛውም የኢትዩጵያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊታይ ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.104 በአሁኑ ወቅት ተፈፃሚነት እንደሌለው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.25/88 ዓንቀፅ 4 መረዳት እንደሚቻለው ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነፃነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች የበረራ ደህንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች የሚታዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለሆነ የወ/መ/ሕ/ስ/ስቁ. 104 ተሽሯል ማለት ይቻላል፡፡

ከክልላዊ ስልጣን ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነገር ቢኖር አንድ ክስ ካንድ ነገሩን ለማየት ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት የመዛወሩ ጉዳይ ነው (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 106) ፡፡ ባለጉዳዩ ጉዳዩን በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይለት ሲፈልግ ማመልከቻውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት የተጠቀሰው የሕጉ ቁጥር ይደነግጋል፡፡ ማመልከቻውን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከተቀበለው ጉዳዩ ክሱን ለማየት ስልጣን ወደ አለው ፍርድ ቤት ወይም ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይዛወራል፡፡ በዚህ አኳኃን ጉዳዩ በወረዳ ፍርድ ቤት

የሚታይ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤት ራሱ ተቀብሎ ሊሰማው ወይም ወደ ሌላ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊያዛውረው ይችላል፡፡

ይህ ዓንቀፅ ድሮ ለነበረው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት ታሳቢ በማድረግ የተቀረፀ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ላለውን የፌዴራል አወቃቀር ስርዓት እንዳለ የሚያገለግል አይመስልም፡፡ ፍርድ ቤቶች በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ የተዋቀሩ በሆናቸው የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄም ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በሆነው ጉዳይ ላይ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጥያቄው መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ክልሎች በውክልናቸው መሰረት በሚያዩት ጉዳይ ላይ ከሆነ ደግሞ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም የክልል ጉዳይ ሲሆን ሁለት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ይኸውም የወረዳ ፍርድ ቤት በያዘው ጉዳይ ላይ ሲሆን ጥያቄው ለሚመለከተው ማእከላዊ ፍርድ ቤት፣ የማእከላዊ (ዞን) ፍርድ ቤት በያዘው ጉዳይ ላይ ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

የሚመለከተው ፍርድ ቤት አንድ ክስ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የቀረበለትን ማመልከቻ የሚቀበልበት አራት ሁኔታዎች እንዳሉ ቁጥር 106 ያመለክታል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) ዝቅተኛው ፍርድ ቤት በልዩ ልዩ ምክንያቶች አድልዎ የሌለበት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት እንደማይችል ግልፅ ሲሆን ፣

ለ) ክሱ በጣም አስቸጋሪና ከባድ የሆነ ለውሳኔ የሚያዳግት የሕግ ጉዳይ ሲኖርበት ፣

ሐ) የክሱ መዛወር ለባለጉዳዮችና ለምስክሮች በቦታው ቅርበትም ሆነ በሌላ ምክንያት ምቹ ወይም ተፈላጊ ሲሆን ፣ እና

መ) በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው በክሱ መዛወር ብቻ ሲሆን ወይም የክሱ መዛወር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ- ስርዓት የተፈቀደ ሲሆን ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- በአንድ ስፍራ አንድ ጧሪ የሌላቸዉ የ70 ዓመት አዛውንት (ሽማግሌ) ከአከባቢው ነዋሪ ህዝብ በእርዳታ ያገኙትን እህል ሰርቀሃል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ስርቆቱ በተፈፀመበት ቀን በሌላ ቦታ ነበርኩ ፣ ነገር ግን የአከባቢው ህዝብ በሽማግሌው መሰረቅ በጣም ስለተቆጣ በሌላ ቦታ እንደነበርኩ የሚያውቁልኝ ምስክሮች የማስፈራሪያ መልእክት ስለደረሳቸው እዚህ ሊመሰክሩልኝ አይችሉምና ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ይዛወርልኝ ሲል ለዞን ፍርድ ቤት ቢያመለክት ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ከተቀበለ ነገሩን ራሱ ሊሰማው ወይም ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ሊያዛውርለት ይችላል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ ሰው የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 644 በመተላለፍ ለአካለመጠን ያልደረሱ ልጆችን የግብረ ስጋ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከልክ በላይ የሚቀሰቅሱ፣ የሚያበላሹ ወይም የሚያነሳሱ ፅሑሮችን አሳይቷል ተብሎ ቢከሰስ ፣ የዚህ ዓይነት ክስ የሚታየው በወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተከሳሹ ለህዝብ ያሳየሁት ፅሑፍ በዓንቀፅ

644 አተረጓጎም "የግብረ ስጋ የተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከመጠኑ በላይ አላነሳሳም" ብሎ ቢከራከር "የግብረ ስጋ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከመጠኑ በላይ ማነሳሳት" የሚለው ከባድ የሆነ የሕግ ክርክር ለመፍጠር ስለሚችል ተከሳሹ ቢያመለክት የዞን ፍርድ ቤት ክሱን ራሱ ለማየት ሊወስን ይችላል፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ በኮምቦልቻ የተጫነ የንግድ ዕቃ የያዘ መኪና በደብሰሲና ወረዳ አልፎ በደብረብርሃን ወረዳ እንደቆመ ዕቃው ተሰርቆ ዓቃቤ ሕጉ ክሱ በደብረሲና ወረዳ እንዲታይ ቢወስንና ተከሳሹና ምስክሮቹ የሚኖሩት በደብረብርሃን ወረዳ በመሆኑ ክሱ ወደ ደብረብርሃን እንዲዛወር ማመልከቻ ቢቀርብ መዛወሩ ለተከሳሹና ለምስክሮች ምቹ ስለሚሆን የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ ይዛወር ብሎ ሊያዝዝ ይችላል፡፡

# ክፍል አንድ

# መደበኛ የወንጀል ክሥ ከመመስረቱ በፊት ውጤታማ የሆነ የፖሊስ ምርመራ መዝገብ አመራር

እንደሚታወቀው ስለ አንድ የወንጀል ጉዳይ ክሥ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ የወንጀል ምርመራ ሥራ የቀጥላል፡፡ ውጤታማ የሆነ የመጨረሻ ግብ ላይ ለመድረስ ግን አንድ ጊዜ ፖሊስ ሥራዬን ጨርሻለሁ ብሎ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 37 መሠረት በተዘጋጀ ራፖር የላከውን የምርመራ መዝገብ ተመልክቶ ከመወሰን ባሻገር በምርመራ ሥራው ላይ ፖሊስና ዐቃቤ ሕግ በመቀናጀት መሥራት ያለባቸው ተግባራት ይኖራሉ፡፡ ይህን ማድረጋቸውም በመጨረሻ ላይ ሊደረስበት የታሰበውን ግብ ውጤታማና አስተማማኝ ከማድረግ አንፃር የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በምርመራ ወቅት ፍርድ ቤቶች የጊዜ ቀጠሮን፣ ዋስትናን፣ ብርበራን ወ.ዘ.ተ በተመለከተ የሚሰጧቸው ትዕዛዛት አንድ የምርመራ ሥራን ፈር ከማስያዝ ባሻገር የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ከማስከበር አንፃር ከፍተኛ ድርሻ ኖራቸዋል፡፡

ከዚህ በታች የሰፈረው ቻርት በቅርቡ እየተደረገ ባለው በፌዴራል መንግስት የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አቤቱታን መመርመር፣ ክሥ መመሥረት፣ መከራከርና ውሣኔ መስጠት የሥራ ሂደት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የፖሊስ የምርመራ ሥራ አካሄድን ነባር የአሰራር ሂደት (AS IS) የሚያሳይ ነው፡፡ ቻርቱን በሚገባ ከተመለከቱ በኋላ በመጨረሻ ላይ በቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቻርቱ በተመለከተው መሠረት ዋና ዋና የምርመራ ሥራ ሂደት ተግባራት የትኞቹ ናቸው?
2. እነዚህን የምርመራ ሥራ ሂደት ተግባራት የሚያቋቁሙ / የሚሸፍኑ የሕገ መንግሥቱንና የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥርዓት ድንጋጌዎች በመሴት ያብራሩ፡፡

3. ከቻርቱ በመነሳት ፖሊስ ውጤታማ የምርመራ ሥራ ለመስራት ምን ማድረግ አለበት ይላሉ?

4. ውጤታማ የሆነ የወንጀል ምርመራ ሥራ ለማከናወን የዐቃቤ ሕግ ድርሻ ምንድነው?

5. ፍርድ ቤቶች በወንጀል ምርመራ ሥራ አካሄድ ላይ የሚኖራቸው ሚና ምንድነው?

### በግል ተበዳዬች፣ ከፖሊስ ጥናት ወይም በዐቃቤ ሕግ በሚሠጠው ትዕዛዝ የሚጀመር ምርመራ[1]




[1] ምንጭ፡- በፌዴራል መንግስት የወንጀል ፍትህ አስተዳዳር አቤቱታ መመርመር፣ ክስ መመሥረት መከራከርና ውሣኔ መስጠት የሥራ ሂደት (ASIS) የካቲት 2001 ዓ.ም


የቴክኒክ ማስረጃዎችና ማመሳከሪያዎችን ማሳባሰብ
ለቴክኒክ (ፎረንሲክ) ምርመራ መላክ
ማመስከሪያ ና ተመርማሪን አረጋግጦ መቀበል
ለባለሙያ መምራት
ባለሙያው የቴክኒክ ምርመራ ያካሂዳል
የምርመራ ውጤቱን አዘጋጅቶ አፅፎ ለኃላፊ አስፈርሞ ማህተም በማስመታት ለመ/ቤት መስጠት
ውጤቱን ከመ/ቤቱ ወጭ በማድረግ ለጠያቂው አካል መስጠት
ውሴቱን ተቀብሎ ገቢ በማኡረግ ለኃላፊው አስመርቶ በመቅድም ላይ በማስፈረም ከመዝገቡ ጋር አያይዞ ቀጣይ ምርመራ መሠራት
የቴክኒክ
ወንጀሉ የተፈፀመበት (አደጋው የደረሰበት) ሥፍራ መሄጃ መኪና መፈለግ ወይም ባለጉዳዩ እንዲያቀርብብ ማድረግ
ወንጀሉ ወደተፈፀመበት ሥፍር መሄድ
ወንጀሉ ከተፈፀመበት ሥፍራ ማስረጃ ማሰባሰብ
የተሰበሰበውን ማስረጃ ዝርዝር መለየት
ለተመርማሪው ማስረጃ በቂ ማመሳከሪያ መፈለግና ለፎረንሲክ ምርመራ መላክ
ወደ ወንጀል ሥፍራ በመድ ቃል መቀበል
ማስረጃ የሆኑትን መሠብሠብ (ፕላን ማንሳትና ክስ መለየት)
ማስረጃ የሚሆኑትን (ምስክሮችን) ቃል መቀበል
በትራፊክ ወንጀል ምርመራ ዋ/ክፍል ክስ መመዝገብ
የስነድና ሌሎች ማስረጃዎችን በማሰባሰብ መዝገቡን አደራጅቶ ለኃላፊው ማቅረብ
ማስረጃ ተሰብስቦ ከተጠናቀቀ በኃላ የምርመራ መዝገብ ውሣኔ እንዲሠጥበት ለኃላፊ ማቅረብ


ኃላፊው ተጠርጣሪው ወይም ኤግዚቢቱን በፖሊስ መጥሪያ ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲያዝ ውሣኔ
የውሳኔ የፖሊስ መጥሪያ እንዲሰጥ ከሆነ
ለተጠርጣሪው መጥሪያ ማዘጋጀት
መጥሪያውን አቅርቦ በኃላፊ ማስፈረም
ደብደቤውን በወንጀል መዝገብ ቤት ወጪ ማስደረግ
ለተጠርጣሪው መጥሪያ በመላክ የቀጠሮውን ቀን መጠባበቅ
አቀረበ
አቀረበ
ውሣኔው የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲወጣ ከሆነ
የፍ/ቤት መያዛ ወይም የመበርበሪያ ትዕዛዝ ለማውጣ ደብዳቤ ማዘጋጀት እና ለኃላፊ አስፈርሞ ወጭ ማድረግ
ደብዳቤውን ለፍ/ቤት ሬጅስትራር ማድረስ
ሬጅስትራር ፋይል እንዲከፍት ማድረግ
ሬጅስትራር የተከፈተውን ፋይል ለችሎት ፀሐፊ መምራት
ችሎት ፀሐፊ ፋይሉን ለችሎት ማቅረብ
ፍርድ ቤት ጉዳዩን መመርመር
ውሣኔ መሥጠት
የተፈቀደ ከሆነ
የተከለከለ ከሆነ


መርማሪው ቃሉን መቀበል
በመዝገብ ላይ ቃሉን በማስፈር ለኃላፊ አቅርቦ ማስወሰን
ውሣኔ
ዋስ
የሚታሰር ከሆነ
የዋስትና ፎርም ሞልቶ መልቀቅ እና ፎርሙን ከመዝገቡ ጋር ማያያዝ
ስለ ቀጣይ አቅራረብ ለመመሪያ ማቅረብ
ኃላፊው ተጠርጣሪው በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲያዝ ውሣኔ መስጠት
በዕለት ሁኔታ እና በእስር መዝገብ ማስመዝገብ
ተፈትሾ እንዲታሰር ለጥበቃ ኃላፊ ማስረከብ
ፍተሻ የግል ንብረቱን መዝግቦ በመያዝ ወደ እስር ክፍል መውሰድ
የጊዜ ቀጠሮ መጠየቂያ ደብዳቤ ማዘጋጀት እና ኃለፊውን አስፈርሞ ወጭ ማድረግ
ትዕዛዝ ተገለብጦ ዳኛ ፈርሞበት ወጭ ሆኖ ለፖሊስ መስጠት
የፍ/ቤት ፋይሉ ተዘግቶ መዝገብ ቤት ማስቀመጥ
ወደ ታክቲክ ምርመራ በመሄድ ተፈላጊው እንዲያዝ ለክትትል ማስተለለፍ፣ ብርበራ ማካሄድ
ክትትል በተጠርጣሪው ላይ ማስረጃ በማሰባሰብ ፍለጋ ማድረግ
የሚያዝ ኤግዚቢት ካሣ በመቅድም ተመዝግቦ ለኢግዚቢት ክፍል መስጠት
ካገኘ ይዞ ለመርማሪ ማስተላለፍ
ካላገኘ ፍለጋውን መቀጠል
ኤግዚቢት ክፍል መዝግቦ ታግ በመለጠፍ ማስቀመጥ


ደብዳቤውን በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ማቅረብ
ሬጅስትራር ፋይል ከፍቶ ለችሎት ፀሐፊ መምራት
ችሎት ፀሐፊው ፋይሉን ለችሎት ማቅረብ
መርማሪው ተጠርጣሪውን በመያዝ ችሎት ቀርቦ ቀጠሮ እንዲፈቀድለት ማስረዳት
ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ መስጠት
ጊዜ ቀጠሮ ካለተፈቀደ
ስለተጠርጣሪ አቆያየት መዝገቡን ለኃላፊ ማቅረብ እና ኃላፊ በሚሠጠው ውሣኔ መሠረት መፈፀም
ተጠርጣሪውን በዋስ (ያለዋስ) ፎርም በማስሞላት መልቀቅ
በመቅድም በማስፈረም የዋስትና ፎርሙን ከመዝገብ ጋር ማያያዝ
ጊዜ ቀጠሮ ከተፈቀደ
ተጠርጣሪውን ይዞ በመመለስ ምርመራ መቀጠል
የዕምነት ቃል ማስጠት የሚያስፈልግ ከሆነ ዳብዳቤ አዘጋጅቶ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ
ደብዳቤውን ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ማቅረብ


ሬጅስትራር ፋይል አስከፍቶ ለችሎት ፀሔፊ መምራት
ችሎት ፀሐፊው ፋይሉን ለችሎት ማቅረብ
ዳኛው የዕመነት ቃሉን ለመ/ቤት ማስተላለፍ
ዐቃቤ ሕግ የዕምነት ቃል ከፍርድ ቤት በመውሰድ ከሌሎች ማስረጃበዎች ጋር ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማዕረብ (ወደፊት)
መርማሪያው የዕምነት ቃል መ/ቁጥሩን በምርመራ መቅድም ማስፈር
መርማሪው የተጠርጣሪውን የጣት አሻራ ሪከርድ አስደርጎ ምርመራ መዝገቡን ማጠናቀቅ
መዝገቡን ለኃላፊው አቅርቦ ማስወሰን
መመሪያ ከተሰጠ በመመሪያው መሠረት ለማሟላት ለኃላፊው ማቅረብ
መዝገቡ ለዐቃቤ ሕግ ይላክ ከተባለ ዋና እና ቀሪ መዝገብ ለይቶ መሸኛ አዘጋጅቶ በማስፈረመ ለመ/ቤት መስጠት
የተጠቀቀ የምርመራ መዝገብ ለዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት እንዲሰጥ ለመዝገብ ቤት ሠራተኛ በማስፈረም ማስረከብ
ምርመራ መዝገቡን ወደ ዐቃቤ ሕግ መላኪያ መዝገብ ላይ መመዝገብ
መዝገቡን ቆጥሮ በማስፈረም ለዐቃቤ ሕግ መ/ቤት ማስረከብ

# ክፍል ሁለት

## የጊዜ ቀጠሮና ዋስትናን የሚመለከቱ ችግሮች

### 2.1 የጊዜ ቀጠሮ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

***ይህንን ንዑስ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ሰልጣኞች፡-***

- የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል የተጠረጠረን ሰው ሰብአዊ መብት ለማረጋገጥ ያለውን ሚና ተገንዝበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነ ስርዓቶችን አውቀው በሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

በወንጀል የተጠረጠረ ሰው በፖሊስ ከተያዘ በኋለ ፍ/ቤት መቅረብ ያለበት ሲሆን የዚህን አሰራር ጠቀሜታና ተጠርቶ ፍ/ቤት ከቀረበ በኋላ የሚፈጸሙ ስነስርዓቶችን እንመለከታለን፡፡

ፖሊስ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ዜጉችን ያለአግባብ በመያዝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከላከል ሐገራት በህግ ከሚያደርጉት ጥበቃ አንዱ በህገ መንግስት መሰረት የተያዘ ሰው ፍ/ቤት በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡፡ በሀገራችንም ይህ መብት በ ሕገ መንግሥስቱ አንቀፅ 19/3 እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 29/1 መሰረት በወንጀል ተጠርጥረው ለተያዙ ሰዎች የተረጋገጠ መብት ነው፡፡

ተጠርጣሪው ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት ወዲያውኑ እንዲቀርብ የሚያስፈልገው የእስሩን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ተጠርጣሪው እንደቀረበ ፍ/ቤቱ ማንነቱን አረጋግጦ ከመዘገበ በኋላ በምን ዓይነት ወንጀል ተጠርጥሮ እንደተያዘ ለተጠርጣሪው ሊገለፅለት ይገባል፡፡ ከዚህ በኋላ ፖሊስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ምክንያቱን ከፖሊስ ማጣራት አለበት፡፡ የተጠርጣሪውም ሐሳብ መሰማት አለበት፡፡ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈቀድበት በቂ ምክንያት ከሌለ እና የተጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስነፍግ ከሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ አለበት፡፡ የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ፖሊስ ያቀረበው ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ ላይ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት የተጀመረ የፖሊስ ምርመራ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ፣ የቀረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ፣ ተጠርጣሪው በእሰር ላይ መቆየት አስፈላጊነት እና የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዚ ለማረጋገጥ ፖሊሱን በመጠየቅ እና እንደአሰፈላጊነቱ የፖሊስ ምርመራ መዝገብን በመመልከት ማጣራት ይጠበቅበታል፡፡

የተጠርጣሪው የመደመጥ መብትን ምንጊዜም ቢሆን መዘንጋት የለበትም፡፡ በተግባር ጥያቄ የሚያስነሣው የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ስልጣን ወሰን ነው፡፡ ችሎቱ ተጠርጣሪው ያለ አግባብ የተያዘ መሆኑን ቢያረጋግጥ ያለ ዋስትና ሊለቀው ይችላል ወይ? የሚለው ያከራክራል፡፡ በህጉ ላይ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ከመፍቀድ እና በዋስትና ከማሰናበት ውጪ የተቀመጠ ሌላ 3ኛ አማራጭ የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ችሎቱ ተጠርጣሪውን በዋስትና ብቻ ነው መልቀቅ ያለበት ሊባል የችላል፡፡ ነገር ግን በስህተት መያዙን ፖሊስ ጭምር እያረጋገጠ ዋሰትና አቅርብ ማለት ትርጉም የለውም፡፡ ዋስትና እራሱን በቻለ የተለየ ክፍል በቀጣይነት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

ከጊዜ ቀጠሮ ችሎት ሥልጣን ጋር በተያያዘ ሌላ ሊነሣ የሚገባው ነጥብ ፖሊስ ምርመራውን ያለበቂ ምክንያት ባያጠናቅቅ ወይም ዓ/ህግ የምርመራ መዝገቡ ደርሶት በወቅቱ ውሣኔ ሣይሰጥበት ቢቀር እና ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን የወንጀል ጉዳይ ዋስትና የሚያስነፍግ ቢሆን የሚፈጠር ሁኔታ ነው፡፡ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ወይም በእስር እንዲቆይ ትእዛዝ ሣይሰጥ የመዝጋት አሰራሩን የሚከተሉ ዳኞች ያጋጥማሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ፖሊስ ተጠርጣሪውን የመልቀቅ ወይም ያለመልቀቅ ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ ተጠርጣሪው ህግን የሚያውቅ ወይም ጠበቃ ካለው ያለው አማራጭ አካልን ነጻ የማውጣት ክስ /habeas corpus/ለፍ/ብሔር ችሎት ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር ሊገመት ለማይችል ሁኔታ ተጠርጣሪውን የሚያጋልጥ ነው፡፡ ተጠርጣሪው ለረጅም ጊዜ በእሥር ላይ ሆኖ ሊንገላታ የሚችልበትን በር ይከፍታል፡፡ ከዚህ የተሻለው አማራጭ ለሚመለከተው ዓ/ህግ ኃላፊ ፍ/ቤቱ በትእዛዝ ለማሣወቅ ወይም በማስጠራት መፍትሔ እንዲገኝ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መንገድ ውጤት ካልተገኘ እስከ መጨረሻ ዓ/ህግ ኃላፊ ድረስ ሁኔታው እንዲታወቅ በማድረግ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡ በሂደት ውስጥ የሥራ ግዴታውን የጣሰ ካለ ለሚመለከተው አካል በማሣወቅ ተጠያቂነት እንዲኖር ማስደረግ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበት እንደነገሩ ሁኔታ ትእዛዝ መስጠት አለበት እንጂ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ጉዳዩን አንጠልጥሎ መተው የህግ የበላይነትን ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ነው የሚሆነው፡፡

ፍ/ቤት ምን ያህል ጊዜ የጊዜ ቀጠሮ ሊፈቅድ እንደሚችልም በህጉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተ ቢሆንም ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ አይገባም፡፡ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳይኖር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በጥንቃቄ እያንዳንዱን ጉዳይ እያጣራ መፍቀድ አለበት፡፡ በአግባቡ ይህ ከተተገበረ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ጠቀሜታ ቢኖረውም የራሱ የሆነ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተጠርጣሪው ከህግ ውጪ ከሌሎች የወንጀል ተሳታፊዎች ጋር በመሆን ሴትን ጠልፎ የደበቀ ቢሆን እና የተጠለፈችው እንዳትለቀቅ የተያዘው ተጠርጣሪ ለመተባበር ባይፈልግ ወይም የተለዩ የተወሳሰቡ ጉዳዮች ቢያጋጥሙ እና ምርመራው በህግ የተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ ባይቻል ሊፈጠር

የሚችለውን አስቸጋሪ ሁኔታ አስቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ 14 ቀን ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ የእረፍት ና የበዓል ቀናትን ያካትታል ወይ? የሚል ጥያቄ በተጨማሪነት ከጊዜ ቀጠሮ አፈ.ቃቀድ ጋር ተያያዞ ይነሣል፡፡ የዋስትና ጉዳይ እራሱን ችሎ በቀጣይነት የሚታይ ቢሆንም ከጊዜ ቀጠሮ ችሎት ጋር ተያይዞ ሣይነሣ መታለፍ የሌለበት አንድ ነጥብ አለ፡፡ ዋስትና በጊዜ ቀጠሮ እና በመደበኛ ሁኔታ ክስ በዓ/ህግ ከቀረበ በኋላ ታይቶ የሚፈቀድበት አሰራር አለ ፡፡ ተጠርጣሪው ከመደበኛ ክስ ከተመሰረተበት በኋላ ባይቀርብ የጊዜ ቀጠሮ በተገባው ዋስትና መሰረት ተከሣሹን እንዴት ማስቀረብ እንደሚቻል በህጉ ላይ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ተከሣሹ ከጠፋበት በጊዜ ቀጠሮ ላይ ዋስትናው የሰው ቢሆንና ዋሱ ሊያቀርበው ባይችል የዋስትናው ገንዘብ ገቢ እንደሆን መታዘዝ ያለበት በጊዜ ቀጠሮው መዝገብ ላይ ነው ወይስ በመደበኛው መዝገብ ላይ፤ ማነው ጥያቄውን አቅርቦ ማስወሰን ያለበት ዓ/ህግ ወይስ ፖሊስ ህጉ ምላሽ የለውም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች መቅረፍ የተዘጋጀው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ረቂቅ አሁን ካለው ህግ መሰረታዊ ልዩነት የሌለውና የህጉን ችግሮች የማይቀረፍ በመሆኑ ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶ ተሻሽሎ ሊያሰራ በሚችል መልኩ መፅደቅ አለበት፡፡ በረቂቁ ላይ ለጊዜ ቀጠሮ የጊዜ ገደብ 6 ወር ተብሎ የተቀመጠ ሲሆን ይህ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ሊታሰብበት ይገባል፡፡ የጊዜ ገደቡ ባይከበርስ ምን ውጤት ይኖረዋል የሚለው ምላሽ ያገኘ ባለመሆኑም እንደገና ሊፈተሽ ይገባል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው ህግ ና ረቂቅ ህግ ያለባቸው ችግሮች በሚገባ ተጠንቶ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ፀድቆ በስራ ላይ መዋል አለበት፡፡

# የመወያያ ነጥቦች

1. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በፖሊስ በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰው እንደቀረበ ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪው በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ከማዘዙ በፊት ወይም በዋስትና እንዲለቀቅ ከማድረጉ በፊት ምን ማድረግ አለበት?
2. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 59/3 መሰረት የሚሰጠው ተጨማሪ የፖሊስ ምርመራ ማጣሪያ የ14 ቀን ጊዜ ከመንግሥት የስራ ቀናት ውጪ የሆኑትን የእረፍት ቀናትና የበአላት ቀን ያካታታል ወይ?
3. ዋስትና በህግ በሚያስነፍግ ጉዳይ ላይ ፖሊስ ያለ በቂ ምክንያት ምርመራውን ሳያጠናቅቅ ወይም ምርመራው ተጠናቆ የምርመራ መዝገቡ ለዐ/ህግ ከተላከ በኋላ በአፋጣኝ ውሣኔ ሣይሰጥበት ቢቀር የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ምን ማድረግ አለበት?
4. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና የሚያስነፍግ የወንጀል ጉዳይ የተጠረጠረን ግለሰብ ያለ አግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ሊለቀው ይችላል ወይ?

5. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ፖሊስ ያለ በቂ ምክንያት ለተጨማሪ ጊዜ ተጠርጣሪውን በእስር ለማቆየት ጥያቄ በማቅረቡ ምክንያት መዝገቡን ተጠርጣሪው እንዲለቀቅ ሳያዝ ወይም ዋስትና ሳይፈቅድ ቢዘጋው በተጠርጣሪው መብት ላይ ምን ዓይነት ተፅእኖ ያሣድራል? የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ተጠርጣሪው በምን መልኩ ህጋዊ መብቱን ማስከበር ይችላል?

6. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት በወንጀል ተጠርጥሮ የተየዘ ሰውን ያለአግባብ መያዙን ቢያረጋግጥ ያለዋስትና ሊለቅቀው ይችላል ወይ?

7. የጊዜ ቀጠሮ ችሎት ተጨማሪ የምርመራ ማጣሪያ የሚፈቅድበትን ጊዜ በህግ ገድቦ መስቀመጥ ምን አይነት ጥቅምና ጉዳት ይኖረዋል፡፡

8. በጊዜ ቀጠሮ ችሎት አንድ ጊዜ ዋስትና ከተገባ በኋላ ምርመራው ተጠናቆ በዓ/ህግ ለፍ/ቤቱ የወንጀል ክስ ሲቀርብለት ሌላ አዲስ የዋስትና ተከሣሹ እንዲያቀርብ ማደረግ ተቀባይነት ያለው አሰራር ነው ወይ?

9. ለዓ/ህግ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ በኋላ የተከሰሰ ሰው በጊዜ ቀጠሮ ችሎት ዋስትና ግዴታ ከገባ በኋላ ቢሰወር መደበኛ ችሎቱ በጊዜ ቀጠሮ ዋስትና ግዴታ ላይ ትእዛዝ ማስተላለፍ ይችላል ወይ?

## 2.2 <u>ዋስትና</u>

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በስተመጨረሻ ሰልጣኞች፡-

- ዋስትና ከሰብአዊ መብት ጋር ያለውን ግንኙነት አውቀው ለተግባራዊነቱ በጽናት ይሰራሉ፤
- ዋስትና የሚፈቀድባቸው እና የሚከለከልባቸውን ምክንያቶች የተነትናሉ፡፡

<u>መርህ</u>፡- የዋስትና መብት ማግኘት ለአንድ በወንጀል ለተጠረጠረ ሰው የተሰጠ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችም የተደገፈ መብት ነው፡፡ ይህ መብት በሀገራችንም ሕገ መንግስታዊ መሠረት ያለው ነው፡፡ የዚህን መብት በተመለከተ በሀገራችን ያለውን ህግ እና አተገባበሩን እንመለከታለን፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2/ ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም ይላል፡፡ የዋስትና መብት ጥያቄ የሚነሳው አንድ ሰው ነፃነቱ በእስር ምክንያት ሲገደብ በመሆኑ በቅድሚያ አንድ ተጠርጣሪ ሊታሰር የሚችልባቸውን ምክንያቶች መመልከት ይገባል፡፡

በሕገመንግስታችን እንደተመለከተውና በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊታሰሩ ይችላሉ። አንድ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው በመከሰሱ ብቻ ሊታሰር ይችላል። ይህ የሚሆነው የተከሰሰበት ወንጀል በዋስ የማያስለቅቀው መሆኑ የተደነገገ ከሆነ ነው። በወንጀል ተከስሶ ወንጀል መፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠበት ሰው ጥፋተኛ በመባሉ ሊታሰር ይችላል። ቅጣት የተወሰነበትም እንዲሁ ከዚህ በተጨማሪ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ሥር በተደነገጉት ምክንያቶችም አንድ ተጠርጣሪ የዋስ መብት እንዳያገኝ ሊያደርጉት ይችላሉ።

አንድ ሰው በመከሰሱ ብቻ ሊታሰር ይችላል ካልን ክስ ቀርበ የሚባለው መቼ ነው? በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ ሁለተኛ መጽሐፍ ክፍል 1 ክስና አቤቱታ ስለማቅረብ በሚለው ሥር ቁጥር 11 ማንም ሰው ወንጀል ሲሰራ ያየ ወይም ያላየም ቢሆን የወንጀል ክስ እንዲቀርብ የማሳወቅ መብትና ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። በቁጥር 13 ሥር ደግሞ ተበደልሁ ባይ ወይም ወኪሉ የክስ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ ያሣያል የወንጀል ክስም ሆነ የክስ አቤቱታ ለፖሊስ ወይም ለዓ/ሕግ ይቀርባሉ (ቁ. 16/1/) ለዓ/ሕግ ከቀረበ (ክሱ ወይም የክስ አቤቱታው/ ምርመራው እንዲካሄድ ለፖሊስ ማስተላለፍ አለበት/16/2/) ፖሊስ በቁ. 22 እና ተከታዮቹ መሠረት ምርመራውን በሚያካሂድበት ሂደት ተጠርጣሪውን የሚይዝበት ሁኔታዎች አሉ። ስለዚህ አንድ ተጠርጣሪ የክስ አቤቱታ ለፖሊስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮም ሊታሰር ይችላል ማለት ነው። በዚህ ጊዜ የታሰረውን ተጠርጣሪ ፖሊስ የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ካልለቀቀው (ቁ. 28) ተጠርጣሪው የዋስ መብቱ እንዲጠበቅለት ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላል (ቁ. 28/2/)

የሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 19(3) የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት እና ለመታሠር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ሊገለጽለት እንደሚገባ ይደነግጋል። የወ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 29ም ተመሳሳይ ድንጋጌ አለው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፍ/ቤት ያልቀረበ ተጠርጣሪ ፍ/ቤት የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት ሊጠይቅ ይችላል። (ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/4) ከዚህም በተጨማሪ የሕገ መንግሥት አንቀጽ 19(6) የተያዘ ሰው በዋስ የመለቀቅ መብት እንዳለው ያሳያል። ይህ በመርህ ደረጃ የተቀመጠ በዋስ የመፈታት መብት ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 17 ጋር ተገናዝቦ ካልታየ የተሳሳተ ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል። ምክንያቱም በዋስ የመፈታት መብት በሕግ በተቀመጡ ምክንያቶች ሊገደብ ይችላልና ነው።

### 2.2.1 የወንጀል ተጠርጣሪ ስለሚያዝበት ሁኔታ

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊያዝ ወይም ሊታሰር አይችልም። (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 49)። ይህ መርህ በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 17 ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ነገር ግን በሕገ መንግሥቱም እንደተጠቀሰው (17.2) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን ለመያዝ ሕግ በፈቀደ ጊዜ መያዝ ይቻላል።

ማንኛውም ሰው ወይም ፖሊስ ከ3 ወር በማያንስ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲፈፀም የተገኘን ሰው (እጅ ከፍንጅ) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ይችላል በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 50 መሰረት ደግሞ ፖሊስ ከአንድ ዓመት የማያንስ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል ለመሥራት የተዘጋጀን ሰው፣ ሰርቷል ተብሎ በሚገባ የተጠረጠረን ሰው፣ የሕዝብን ፀጥታ በማበላሸት ላይ የሚገኘን ሰው፣ ፖሊስ ሥራውን በሚሠራበት ወቅት የሚከላከለውን ሰው፣ ለማምለጥ የሞከረን እስረኛ፣ ከፖሊስ ወይም ከወታደርነት የከዳን ሰው፣ ሕግ ያልፈቀደለትን የቤት መሠርሠሪያ ይዞ የተገኘን ሰው፣ የተሰረቀ ዕቃ የያዘ ሰው፣ ወይም ወንጀል በመፈፀም ረገድ ያገኘው ዕቃ በይዞታው የተገኘበት ሰው፣ አደገኛ ሥራ ፈት መሆኑ የተጠረጠረን ሰው፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ ይችላል (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.51(1))፡፡

ሌሎች በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት (ለምሣሌ የፀረ ሙስና ኮሚሽን) ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አንድን ተጠርጣሪ መያዝ ይችላሉ፡፡ (51/2/)

›ፖሊስም ሆነ ሌሎች ተጠርጣሪን ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመያዝ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተጠርጣሪውን በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ ግን አለባቸው (የፀረ ሙስና አዋጅ ቁ. 235/93 አንቀጽ 7/6/) ከ48 ሰዓት በላይ ለማዘግየት የሚቻለው ተጠርጣሪውን በአቅራቢያው ወደ ሚገኝ ፍ/ቤት ለማቅረብ የቦታ ርቀትና የመገናኛ ሁኔታ ከገደቡ ብቻ ነው (የህገ መንግስቱ አንቀጽ 19/3/; የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 29/1/፡፡

### 2.2.2 <u>የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ስለመልቀቅ</u>

ከላይ እንደተገለፀው ፖሊስ የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቀው ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ ወንጀሉ በጽኑ እሥራት የማያስቀጣ ሊሆን ወይም ደግሞ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.28)

ፖሊስ በወንጀል ጠርጥሮ በመያዝ ለፍ/ቤት ያቀረበውን ተጠርጣሪ ፍ/ቤቱ በዋስትና ወረቀት ሊለቀው ይችላል (59/1/)፡፡ ይህን የሚያደርገው ተጠርጣሪው የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የማያስከለክለው፣ ምርመራ እየተካሄደበት ከሆነ መለቀቁ በማስረጃ ማሰባሰቡ ሂደት ላይ እንቅፋት የማይፈጥር፣ ቢለቀቅ ግዴታውን አክብሮ የሚቀርብ መሆኑን፣ መለቀቁ ለሕዝብ ፀጥታና ሠላም አስጊ አለመሆኑና ሌላ ወንጀል የማይፈጽም መሆኑን በማገናዘብ ሊሆን ይገባል፡፡

የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 63 የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል የሞት ቅጣትን ወይም 15 ዓመት ወይም በላይ የሆነ ጽኑ እሥራት የማያስቀጣው ከሆነና ወንጀል የተፈፀመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የማይሞት የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤት የዋስትና ወረቀት አስፈርሞ ሊለቀው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

በዋስትና ለመለቀቅ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ፍ/ቤት ቶሎ ውሣኔ መስጠት እንዳለበት የሚደነግገው ደግሞ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 66 ነው፡፡ በዚህ ሕግ መሠረት ፍ/ቤቱ ማመልከቻው በደረሰው 48 ሰዓት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ከውሣኔው በፊት የዓ/ሕጉን ወይም የመርማሪውን ሃሳብና ትችት እንደሚጠይቅ ያስቀምጣል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ግን ይህ ሕግ ብዙ ጊዜ ሲተገበር አይታይም፡፡ በዋስትና ማመልከቻው ላይ ሃሳብ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡ በእጁ ስለሌለ የምርመራ መዝገቡን ከፖሊስ ወስጄና ተመልክቼ አስተያየቴን ለማቅረብ ጊዜ ያስፈልገኛል ይላል፡፡ ፍ/ቤቱም ማመልከቻውን ከዓ/ሕግ አስተያየትና ከምርመራ መዝገቡ ጋር መርምሮ በተሰጠው የ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ለመስጠት በተግባር ችግር አለ ይላል የዋስትና ጉዳዮችን ለብቻው የሚያዩ ችሎቶች ባለመኖራቸው ዳኞች የጊዜ ገደቡን አክብረው ውሣኔ ለመስጠት ሲቸገሩ ይታያል፡፡

የዋስትና መብት ጥያቄ መሠረታዊ ከመሆኑ አንፃር ሕጉ ሊተገበር ይገባል፡፡ ክስ ለፍ/ቤት በቀረበበት ጉዳይ ከሆነ ዓ/ሕግ የምርመራ መዝገቡን አይቶ ክስ የሚያዘጋጅ እንደመሆኑ ከሕጉ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ ጉዳዩን የሚያራዝም የተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅና ሊፈቀድለት የሚገባ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ውስብስብ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ዳኞችና ዓ/ሕጎች ፍትህ እንዳይጓደል በጥንቃቄ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ክስ በፍ/ቤት ያልተመሠረተበት ጉዳይ ከሆነም መርማሪው ምርመራ መዝገቡ በእጁ ያለ/ የነበረ እንደመሆኑ ወዲያውኑ አስተያየቱን ለመስጠት ይቸገራል ሊባል አይችልም፡፡ ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የዋስትና ማመልከቻ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በአጭር ጊዜ እንዲወስኑ ሕግ የሚጠይቅ በመሆኑ ቅድሚያ ሰጥተው ሊወስኑ ይገባል፡፡

ሌላው በዋስትና ዙሪያ ትኩረት የሚሻው በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 67 ሥር የተደነገገው ነው በዚህ ሕግ መሠረት ዋስትና የጠየቀን ተጠርጣሪ ማመልከቻ መቀበል የማይቻለው:-

ሀ/ በዋስትና ወረቀቱ የተመለከቱትን ግዴታዎች የማይፈፀም ነው ተብሎ ሲገመት፤

ለ/ ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፤

ሐ/ ማስረጃ ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ሲታሰብ ነው፡፡

ተጠርጣሪው የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትና የማይከለከል ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱትን የማያሟላ ተጠርጣሪ የዋስ መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ በዋስትና ወረቀት የሚገለፀው ዋነኛው ግዴታ በቀጠሮ ቀን ያለመቅረት ነው፡፡ ተከሳሹ ተመልሶ ወደ ፍ/ቤት የማይመጣ ነው ተብሎ ከተገመተ አይለቀቅም፡፡ ህብረተሰብን በተጠርጣሪው ሊፈፀም ይችላል ከሚባል ተጨማሪ ወንጀል ለመጠበቅ ሲባልም ዋስትና ሊከለከል ይችላል፡፡ ሌላው ተጠርጣሪው ከዓ/ሕግ ማስረጃዎች ጋር ካለው ቀረቤታም ይሁን በሌላ

ምክንያት ማስረጃ ያጠፋል፣ ምስክሮች ሊያባብል ይችላል የሚል ግምት ካለም የዋስትና መብቱ ተጠቃሚ ላይሆን ይችላል ማለት ነው፡፡ በዚህ የሕግ አንቀጽ ሥር ከ ሀ-ሐ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ለመቀበል ሕጉ ጥያቄው የቀረበለት ፍ/ቤት ግምት ብቻ በቂ መሆኑን ያሳያል "ግዴታዎቹን የሚፈጽም የማይመስል" የሚለው ሐረግ ግምትን ያመለክታል፡፡ ይህ ማለት ግን ፍ/ቤት ከተባለው ግምት ላይ ለመድረስ ምንም መነሻ ሳይኖረው በዘፈቀደ የሚወሰነው ነው ማለት አይደለም፡፡ ለምሣሌ ያህል አንድ ተጠርጣሪ የዋስ መብቱ እንዲከበርለት ለፍ/ቤቱ ሲያመለክት ዓ/ሕጉ ወይም መርማሪው ተጠርጣሪው ተደብቆ ከሀገር ሊወጣ ሲል መያዙን ቢያረጋግጥና በዋስትና መለቀቁን ቢቃወም ፍ/ቤቱ ይህ ተጠርጣሪ/ተከሳሽ ቢለቀቅ አይመለስም ብሎ ለመገመት በቂ መነሻ ምክንያት አለው ማለት ይቻል ይሆናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ተከሳሹ ዋስትና የተነፈገበት ምክንያት ከተለወጠ በኂላም ያላግባብ የሚታሰርበት አጋጣሚ አለ፡፡ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሐ/ ሥር ማስረጃ ያጠፋል፣ ምስክር ያባብላል ተብሎ የታሰረ ተከሳሽ ማስረጃዎቹ ተሰብስበው ካለቁ በኂላ እሥሩ ሊቀጥል የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡

ተጠርጣሪ/ ተከሳሽ ያቀረበው በዋስ የመለቀቅ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ተከሳሹ ዋስ እንዲጠራ ወይም ገንዘብ እንዲያስይዝ ይታዘዛል (የወ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 68)፡፡ ነገር ግን የዋስትና ልክን በመወሰን ረገድ ለተመሳሳይ ጉዳዮች በተለያዩ ችሎቶች/ዳኞች ዘንድ ያለው ልዩነት ከፍተኛ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንደአብነት የሚጠቀሰው በቀድሞው የወ/መ/ሕ/ቁ. 526 ሥር በቸልተኝነት ሰው መግደል ለሚከሰሱ ሰዎች የሚጠየቀው የዋስትና ገንዘብ መጠን ነው፡፡ አንዱ ችሎት ከብር 500 የማይበልጥ ዋስትና ሲጠይቅ በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ ችሎት ብር 5 ሺ ሲጠይቅ ማየት በጣም የተለመደ ነበር፡፡ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ሥ/ቁ. 69 ሥር ፍ/ቤት የዋስትና ገንዘብ መጠንን በመሰለው እንደሚወስን ቢደነገግም የወንጀሉን ከባድነት፣ ተከሳሹ ከቀጠሮ የማይቀር መሆኑን የተከሳሹንና የዋሱን ሀብት መጠን፣ ሲለቀቅ ያለውን አደጋ (በህዝብ ፀጥታ ላይ) ማገናዘብ እንደሚገባም ሠፍሯል፡፡

ለአንድ ተከሳሽ የዋስትና ወረቀት ፈርሞ ዋስ የሆነ ሰው ተከሳሹ በየቀጠሮው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

የዋስትና ግዴታ የሚገባ ሰው ይህ ግዴታው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በፍርድ ቤት ይወሰናል፡፡ ይህ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የሠፈረ ቢሆንም ( ቁ. 71) ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሲጠቀሙበት አይታይም፡፡ የዋስትና ወረቀት ፈርሞ ግዴታ የገባ ሰው ፍርድ ቤት ግዴታው የሚቆይበትን ጊዜ ካልወሰነ ጉዳዩ ዕልባት እስኪያገኝ ድረስ ይቆያል፡፡ ነገር ግን ተጠርጣሪ/ ተከሳሽ በዋስ ከተለቀቀ በኂላ እንደገና ከተያዘ ወይም ዋሱ የዋስትና ግዴታውን ፍርድ ቤት ቀርቦ ካወረደ ጉዳዩ ከማለቁ በፊትም ግዴታው ቀሪ ሊሆን ይችላል፡፡

በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 71/2/ መሠረት የዋስትናው ግዴታ የሚቆይበትን ጊዜ የመወሰን ልምድ ባለመኖሩ አንዳንዴ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህን ለማሳየት በሽግግሩ ዘመን የተፈጠረን ሁኔታ መጥቀሱ ጠቃሚ ነው፡፡ በአዋጅ ቁ. 22/84 የተቋቋመው የልዩ ዓ/ሕግ ጽ/ቤት በሥልጣኑ ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በሚመረምርበት ወቅት በወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎችን የመያዝ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ሁኔታ የታሰሩ ሰዎች በፍርድ ቤት የአካል ነፃ ማውጣት አቤቱታዎችን ሲያቀርቡ ዓ/ሕጉ ግለሰቦቹ የማይፈቱበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍ/ቤቶች በዋስ በርካታ ሰዎች እንዲፈቱ አድርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል ያልነበሩ ዓ/ሕግ ክስ ሳይመሰረትባቸው ለዓመታት የቆዩ ወይም ጭራሹንም ክስ ያልተመሰረተባቸው ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የዋስትና ወረቀት ፈርመው ግዴታ የገቡ ዋሶች የዋስትና ግዴታቸው የሚቆይበት ጊዜ ባለመወሰኑ በተለይ ንብረታቸውን ለዋስትናው ያስያዙ፣ ሰዎች ዋስ ከሆነ ከዓመታት በኋላ እንኳን ንብረታቸውን ለመሸጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለማስተላለፍ የተቸገሩበት ሁኔታ ነበር፡፡

ስለሆነም ፍ/ቤት በተለይ ከክስ በፊት የዋስ መብታቸውን ለሚጠብቅላቸው ተጠርጣሪዎች የዋሶቹን የግዴታ ጊዜ በመወሰን የዋሶቹ የግዴታ ጊዜ ያላግባብ እንዳይራዘም ስለሚያደርግ የወንጀሉን ከባድነትና ነባራዊውን ሁኔታ በማገናዘብ ሕጉን መተግበሩ ጠቃሚ ነው፡፡

የዋስትና ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ ተጠርጣሪ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሀያ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን (በቁ. 75) ይህን አንቀጽ አስመልክቶ የሚነሳው ጥያቄ ይግባኝ ለማለት የተፈቀደው ለተከሳሽ/ ተጠሪጣሪ ብቻ ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ የዋስ መብት ጠይቆ ሊከለከል የሚችል ተከሳሽ/ ተጠርጣሪ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከሳሽ ያለውን መብት ለማሳየት ሕጉ በዚህ መልክ የተቀረፀ እንጂ የዋስ መብት በማይፈቅድ ወንጀል የተከሰሰን ሰው በፍ/ቤት በዋስ ቢለቀቅ ዓ/ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ የሚከለክለው አይደለም፡፡

ፍ/ቤት በዋስ የለቀቀውን ሰው መልሶ ማሰር ወይም ሌላ ዋስ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ የሚከሰተው በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ ዋሱ ቢሞት፣ ከሀገር ቢጠፋ፣ ወይም ግዴታውን ሊወጣ የማይችል መሆኑ ሲታወቅ ወ.ዘ.ተ…

ተከሳሽ ዋስ ጠርቶ ከእስር ከተለቀቀ በኋላ በቀጠሮው ቀን ባይቀርብ እንዲያዝ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ዋሱም የዋስትና ግዴታ የገባበትን የገንዘብ መጠን ለመንግሥት ገቢ የማያደርግበት ምክንያት ካለው ቀርቦ እንዲያስረዳ ይጠየቃል፡፡ ካላስረዳ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ ይታዘዛል (ቁ. 76)፡፡ ከእዚህ መገንዘብ የሚቻለው ዋሱ ግዴታ የገባበትን ገንዘብ ከመክፈል ያለፈ ሌላ ተጠያቂነት እንደሌለበት ነው፡፡ በሕጉ ከተመለከተው ውጭ ዋሱን ተከሳሹን ይዘህ ቅረብ ማለትም ሆነ ዋሶችም የግዴታቸውን ወሰን ባለመረዳት ፍ/ቤት ቀርበው ተከሳሹን ይዘው ለመቅረብ እንዲችሉ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ተገቢ አይደለም፡፡

# የመወያያ ጥያቄዎች

1. አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የዋስትና ጥያቄ ቢያቀርብ በዋስትና እንዲለቀቅ የዋስትና ግዴታውን አያከብርም ብሎ ለመገመት መነሻዎቹ ምንድናቸው?

2. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ .75 ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ እንዳይጠይቅ ይከለክላል ወይ?

3. የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ላይ የተጠቀሰውና ዋስትና የሚያስከለክለው ወንጀል መነሻ ቅጣቱ 15 ዓመት የሆነው ነው ወይንስ መነሻ ቅጣቱ ዝቅተኛም ቢሆን ቅጣቱ 15 ዓመት የሚደርሰው ሁሉ?

4. በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 63 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች በአንድ ላይ መሙዋላት አለባቸው ወይስ በተናጠል(cumulative or alternative requirements)?

5. ዋስትናን ለማስተናገድ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 64/2 መሰረት የግድ ጥያቄው በጽሁፍ መቅረብ የለበትም ወይ?

6. በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 63/2 መሰረት በማንኛውም ጊዜ እራሱ ተከሳሹ ከሚያቀርበው ዋስትና በተጨማሪ ለራሱ የዋስትና ግዴታ ሁል ጊዜ መፈረም አለበት ወይ?

7. በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 63 የተመለከተውን የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ስለዋስትና መብት ካሰፈረው ድንጋጌ አንፃር እንዴት ይመለከቱታል?

## ክፍል ሦሥት

## በዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዛትና ውሣኔዎች

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ ምርመራ መዝገብ ተፈፀመ በተባለ ወንጀል ላይ ከተጣራ በኋላ ቢደርሰውም የወንጀል ክስ ለፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት ሕጉ ክስ ማቅረብን የሚከለክልባቸውን ሁኔታዎች መኖራቸውን በሚገባ ሣያጣራ ክስ ማዘጋጀት ና ለፍ/ቤት ማቅረብ የለበትም። ክስ ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ ነው መሆን ያለበት።

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንደደረሰው በበቂ ሁኔታ ያልተጣሩ ነገሮች ካጋጠሙት መዝገቡን መልሶ ለተጨማሪ ምርመራ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.38/ሕ መሠረት መመለስ አለበት። ክስ ለማቅረብ የሚያጠራጥር ነገር ካጋጠመ የበላይ ዐቃቤ ሕግ መመሪያ እንዲሰጥበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሠረትም መተላለፍ አለበት።

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 39 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብን መዝጋት አለበት። እነዚህም ክስተቶች የተከሣሹ መሞት፣ የዕድሜው ከዘጠኝ ዓመት በታች መሆን፣ በዓለም አቀፍ ሕግ የዲኘሎማቲክ ከለላ መኖር እና በልዩ ሕግ መብት የተሰጠው መሆን ናቸው።

በዐቃቤ ሕግ ክስ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሌሎች ምክንያቶች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 42 ሥር ተዘርዝረዋል። ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ማስረጃ ከሌለ ክስ መቅረብ የለበትም። ማስረጃው መመዘን ያለበት ጥፋተኛ ለማስደረግ ከማስቻሉ አንፃር ነው። አንድን ወንጀል ለማቋቋም ከሚያስፈልጉት ወሣኝ ነገሮች አንዱ የሆነው የፍሬ ነገር ሁኔታ መኖር ሣይረጋገጥ በምንም ዓይነት ሁኔታ ክስ መቅረብ የለበትም። ለምሣሌ ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡት ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ከሆነ ክስ ቀርቦ ፍ/ቤትም ቢቀርቡ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ዐቃቤ ሕግ በጥንቃቄ በፖሊስ የምርመራ መዛግብት ውስጥ የሚገኙ ማስረጃዎችን አንዱን ከሌላው ጋር እያነፃፀረ በመመዘን ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ ተመልክቶ ክስ ለፍ/ቤት ቢቀርብ ውጤቱ ምን ለሆን እንደሚችል በማገናዘብ መወሰን አለበት። የሕጉ አቀራረፅ ምንም ችግር የሌለበት ሆኖ ሣለ በረቂቁ ሕግ ላይ ጥፋተኛ ለማድረግ የሚለው ሀረግ እንዲወጣ መደረጉ ተገቢነት የለውም። ጥብቅ መሥፈርትን ያስቀመጠው ሕግ እያለ እንኳን ሣይጣራ ክስ ሲቀርብ ይስተዋላል። የባሰ የበለጠ የላላ መሥፈርት ማስቀመጡ በበቂ ሁኔታ ያልተጣሩ ክሶች ለፍ/ቤት እንዲቀርቡ በር የሚከፍት በመሆኑ ረቂቁ ሕግ ሊስተካከል ይገባል። የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮም የሚሳየው ጥፋተኝነትን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ከሌለ ክስ መቅረብ እንደሌለበት ነው።

የተከሰሰውን ሰው ለማግኘት የማይቻል ከሆነ ና ጉዳዩም በሌለበት ሊታይ ካልቻለ ክስ ማቅረብ ትርጉም አይኖረውም። በተለይ በዐቃቤ ሕግ በወቅቱ ክስ ተዘጋጅቶ ሣይቀርብ ጊዜ ካለፈ ክስ ከመቅረቡ በፊት በቅድሚያ የተከሣሹ መኖር መጣራት አለበት። ክሱ ከቀረበ በኋላ ፍ/ቤት ያፈላልገው በሚል ሂሣብ ክሱ ከቀረበ ትርፉ ያለ አግባብ የራሱም የዐቃቤ ሕግን ጨምሮ የሕዝብና የመንግሥት ጊዜ ና ሀብት ያለ አግባብ እንዲባክን ማድረግ ነው። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት ተከሣሹ ሊገኝ መቻል አለመቻሉንና ጉዳዩም ተከሣሽ በሌለበት ሊታይ መቻሉን ማረጋገጥ አለበት።

በይርጋ በታገደ ወይም ለተፈፀመው ወንጀል ምህረት (amnesty) ተደርጐ እንደሆነም ክስ ማቅረብ አይቻልም። በህገ መንግስቱ አንቀፅ 28/1 መሠረት ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰው ዘር ማጠፋት፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት ዕርምጃ የሚወስድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሣኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም። ይቅርታ (pardon) በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የሚመጣ በመሆኑ ከክስ ማቅረብ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የለውም።

ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ ያሉት በሙሉ ቀደም ብሎ በሕግ የተሻሩ ናቸው፡፡ በአስፈፃሚው ትዕዛዝ ክስን የማቋረጥ አሠራር የዐቃቤ ሕግን ነፃነት ለማስጠበቅ በአዋጅ ቁጥር 39/85 እንዲሻር ተደርጓል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም ምክንያት መዝገብ ሲዘጋ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ለፖሊስና ለተበዳይ ማሣወቅ እንዳለበት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 39/4 እና 43/2 ሥር ተደንግጐ ስለሚገኝ ሁልጊዜ መተግበር አለበት፡፡ ይህ ግልፅነተ ና ተጠያቂነትን ለማስፈን ወሣኝ አሠራር በመሆኑ ሊታለፍ አይገባም፡፡ በተለይ ለተበዳይ ማሣወቁ ቅር ከተሰኙ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ አቤቱታውን በማቅረብ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ሊያስደርግ ስለሚችል ማስተላለፍ አለበት፡፡ እራሱ የተበደለ ሰው ቀርቦ እስኪጠየቅ መጠበቅ የለበትም፡፡ በፖሊስ አማካኝነት ወይም በቀጥታ በአድራሻው ለተበደለው ወገን የዐቃቤ ሕግ ውሣኔ ሊገለፅለት ይገባል፡፡ እስከ መጨረሻው የዐቃቤ ሕግ ኃላፊ ድረስ በተዋረድ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገልጋዮች ቅሬታቸውን እንዲያቀርቡ የሚያስችል ምቹ አሠራር መዘርጋት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የወንጀል ክስ አቀራረብንና ክስ ማሻሻልን የሚመለከቱ ችግሮች

ዐቃቤ ሕግ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 38/ሀ እና 40 መሠረት ክስ ለማቅረብ የወሰነ እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. ከ108-122 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ የወንጀል ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣኑ የሌለው ፍ/ቤት ክሱ ከቀረበለት መቀበል የለበትም፡፡ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበን ጉዳይ መመለስ የማይችለው ወንጀሉ በወ/ሕ/አ 665 ሥር የሚወድቀውን ስርቆትን የተመለከተ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመው ከፍተኛው ፍ/ቤት ዝም ብሎ ጉዳዩን ማስተናገድ አለበት፡፡

ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመው ሌላው ችግር የተወሰኑ ወንጀሎች በአንዱ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ሥር ሌሎቹ ደግሞ በሌላ ፍ/ቤት ሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ሲሆን በምን ዓይነት ሁኔታ መስተናገድ አለባቸው የሚለው ነው፡፡ ለምሣሌ በወ/ሕ/አ 635 ስር በስርቆት የተከሰሰ ሰው በተጨማሪ በደንብ መተላለፍ በወ/ሕ/አ 309 መሠረት የሚያስጠይቀውን ስለት ነገር ወይም በወ/ሕ/አ 854 ስር የሚያስጠይቀውን አጠራጣሪ ነገር ይዞ ቢገኝ ክሶቹ የት መቅረብ አለባቸው የሚለው ሊያወዛግብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን የመመልከት ሥልጣን የተሰጠው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የከተማው ፍ/ቤት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የበታች ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከከተማው ፍ/ቤት ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቀርብ ጉዳይ የለም፡፡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 109/3 መሠረት የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ወንጀሎቹን ጠቅልሎ ለማየት ሥልጣን ያለው የበላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንዲመለከት ነው የሚደነግገው፡፡ በክልልም ቢሆን የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በወረዳ ፍ/ቤቶችና የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ካላቸው በቀበሌ

ማህበራዊ ፍ/ቤት መሀከል ሊከሰት ይችላል። አሁን ያለውም ሕግ ሆነ ረቂቁ ሕግ ለዚህ ግልፅ ምላሽ የላቸውም።

ዐቃቤ ሕግ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ከደረሰው በኋላ በ15 ቀን ውስጥ ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት። የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት። የክሱ ይዘት ሕጉ ያስቀመጠውን ድንጋጌና ፎርም መከተል አለበት። ከይዘቱ ጋር ተያይዞ የሚነሣው አንዱ ችግር ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111/1/ሐ ሥር የተጠቀሰው ጊዜ የሚለው ቃል ነው። አንዳንዶች ጊዜ ሰዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ የጊዜ ክፍፍሎች እያንዳንዳቸው በክሱ ላይ ካልተዘረዘሩ ክሱ ተቀባይነት ለኖረው አይገባም። የተከሣሹን የመከላከል መብት ያጣብባል። ፍ/ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይገባል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ።

በሌላ በኩል የሚነሣው ክርክር ሕጉ የሚለው ጊዜ ነው። ጊዜ ደግሞ በተለያየ መልክ ሊገለፅ ይችላል። እያንዳንዱን የጊዜ ክፍልፋይ የሚቻል ሆኖ ማስቀመጥ ከተቻለ ጥሩ ነው። ነገር ግን ሰዓትና ቀን አልተጠቀሰም ብሎ ከወዲሁ ክሱን ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ጊዜ ተሟልቶ ባለመጠቀሱ ብቻ ክሱ ከወዲሁ በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ሊሆን አይገባም። እያንዳንዱ ጉዳይ ክሱን ለማስረዳት ከቀረበው ማስረጃ አንፃር መታየት አለበት የሚል ክርክር ይቀርባል።

በማኀበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ሁኔታውን ለማሣየት ያክል አንድ አባት የሦስት ዓመት ህፃን ልጁን ለማሣደግ ከባለቤቱ ጋር በፍ/ቤት ሲፋታ ተረክቦ እቤቱ ከወሰዳት በኋላ በመደብደብ አካሏ ላይ ከፍተኛ ጊዳት ቢያደርስና ከወራት ቆይታ በኋላ ጉዳዩ ተደርሶበት ሲከሰስ ተበዳይዋ ህፃን ሰዓቱን፣ ቀንና ወሩን አስታውሣ መግለፅ ብትቸገር ጉዳዩ እንዴት መስተናገድ አለበት የሚለው ሊያነጋግር ይችላል። ተበዳይዋ ህፃን በደሉን ያደረሰባት አባቷ መሆኑን ካስረዳችና ጊዜውን ግን ካላስታወሰች በዚህ ምክንያት ብቻ ውድቅ ማድረግ ኢፍትሃዊ ነው የሚሆነው። ዐቃቤ ሕግ ክሱ ላይ በፖሊስምርመራ ጊዜ ሊታወቅ ያልቻለን ጊዜ ሊጠቅስ አይችልም። በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ሰዓቱ ቀነ -ና ወሩም ባለመጠቀሱ ብቻ የተከሣሹ መብት ይጣበባል ማለት አስቸጋሪ ነው። በዐ/ህግ ወንጀል መፈጸሙ ከተረጋገጠ ተከሣሹ ሕፃኗን በአግባቡ ይዞ ይንከባከብ እንደነበረ ማስረዳት አለበት። በደሉ በሌላ ሰው ደረሰ የሚልም ከሆነ ይህንን ማረጋገጥ አለበት። ኃላፊነቱ የራሱ ነው። የጊዜው ክፍልፋይ አልታወቀም በሚል ምክንያት ብቻ ክሱ ውድቅ ሊሆን ፈፅሞ አይገባም። እንደነገሩ ሁኔታ የቀረበውን ክስ ከሕጉና ከማስረጃው አንፃር መመዘን አለበት። በረቂቁ ሕግ ላይም የሕጉ አቀራረፅ ተመሣሣይ ነው።

በወ/ሕ/አ 23 መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው። እነዚህ ሶስት መሠረታዊ መስፈርቶች በክሱ ላይ ተገልፀው መመልከት እንዳለባቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 ስር ተደንግጓል። ይህንን ለይቶ አብራርቶ ማስቀመጥ እንደቀላል የሚታይ ነገር አይደለም። ዐቃቤ ሕግ ክስ ከማቅረቡ በፊት ተጣሰ የተባለ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መኖሩን እና የወንጀሉን ማቋቋሚያ መስፈርቶች የአዕምሮ ሁኔታና

ግዙፋዊ ተግባራትን መለየት አለበት፡፡ በዚህ መልኩ በጥንቃቄ ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም፡፡ አይገባም፡፡ እንደነገሩ ሁኔታ የቀረበውን ክስ ከሕጉና ከማስረጃው አንፃር መመዘን አለበት፡፡ በረቂቁ ሕግ ላይም የሕጉ አቀራረፅ ተመሣሣይ ነው፡፡

አንድ ሰው ሌላውን በጥፊ ቢመታውና በአካሉ ላይ ፊቱ ከመቅላቱ ውጪ ምንም ጉዳት ባይደርስ ክሱ መቅረብ ያለበት በወ/ሕ/አ 560/1 መሠረት በእጅ ዕልፊት ነው ወይስ በወ/ሕ/አ 840 መሠረት በደንብ መተላለፍ ሊያወዛግብ ይችላል፡፡ በተመሣሣይ በወ/ሕ/አ 665 ሥር መውደቅ ያለበት የስርቆት ተግባርና በወ/ሕ/አ 852 መሸፈን ያለበት ቀላል ስርቆት ልዩነት በተጨባጭ አንዳንድ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለመለየት አስቸጋሪ ነው፡፡ እንደ ነገሩ ሁኔታ በአግባቡ እየታየ ክስ መቅረብ አለበት፡፡

ክሱ ሲዘጋጅ ስህተቶች የተሠሩ እንደሆነ ዋጋ አያስጡትም፡፡ ነገር ግን ስህተቱ መሠረታዊ ከሆነ ወይም ተከሣሹ ሊያሣስት የሚችል መሆኑ ከታመነበት ክሱ እንዲሻሻል መደረግ አለበት፡፡ ክስን ቀላል አንቀፅን ወደ ከባድ ቀይሮ ለማሻሻል የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ስህተት እስከተፈፀመበት ድረስ መስተካከል አለበት፡፡ በአፃፃፍ ምክንያት ለሚፈጠሩ አነስተኛ ስህተቶች ተብሎ ክሱ እንደገና መሻሻሉ ተገቢ አይመስልም፡፡ ዐቃቤ ሕግ ና ተከሣሽ ወይም ጠበቃው ከተግመኑ በቀላሉ በችሎት በዐቃቤ ሕግ ሊስተካከሉ የሚችሉ ግድፈቶች መታረም አለባቸው፡፡ ክስ ስህተት በተገኘ ጊዜ ሁሉ መስተካከል አለበት፡፡ በቀላል መስተካከል የሚችል ጉዳዮች አዲስ ክስ እንደገና ይዘጋጅ ማለት ምክንያታዊ አይመስልም፡፡ ጠቃሚው ነገር ዐቃቤ ሕግ ክሱን አዘጋጅቶ ሲያቀርብ በተቻለ መጠን ስህተቶች እንዳይፈጠሩ መጠንቀቅ መሆን አለበት፡፡ ክሱ በተስተካከለ ወይም አዲስ ክስ በተጨመረ ቁጥር ለተከሣሹ ተነቦለት እንዲረዳው መደረግ አለበት፡፡ የተለየ መቃወሚያ ካለ ወይም መታመኑና መካዱ በድጋሚ መረጋገጥ አለበት፡፡ ምክንያቱም በክሱ ላይ የተደረጉትን ለውጦች ተከትሎ ተከሣሹ የተለየ መቃወሚያ ለያቀርብ ይችላል፡፡

ከዐቃቤ ሕግ ክስ አቀራረብ ጋር ተያይዞ ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላው ነጥብ ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሕግ አንቀፅ ጉዳይ ነው፡፡ ነገሩን በምሣሌ ለማስረዳት በወ/ሕ/አ 628/ሀ መሠረት ክስ የሚቀርበው በወ/ሕ/አ 620 እስከ 627 የተመለቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ተፈፅሞ እርግዝና ከተከተለ እና በእነዚህ በቀጥታ በተጣሱት ድንጋጌዎች ውስጥ የተቀመጠው ቅጣት ከወ/ሕ/አ 628/ሀ ካነሰ ነው፡፡ የ16 ዓመት ልጅ ተገዳ ብትደፈር ተገቢነት የሚኖረው የሕጉ አንቀፅ 620/2/ሀ ነው፡፡ ይህችው ህፃን ሣትገደድ የግብረሥጋ ግንኙነት ብትፈጽም ወንጀሉ የሚወድቀው በወ/ሕ/አ 626/1 ሥር ነው፡፡ በአጋጣሚ ህፃኗ ለእርግዝና ብትዳረግ ተገቢነት የሚኖረው የበለጠ ቅጣት ከሁለት የድንጋጌዎች በላይ የሚያስቀጣ የወ/ሕ/አ 628/ሀ ነው፡፡ ክስ ሲቀርብ የወ/ሕ/አ 626/2/ሀ እና 628/ሀ ወይም 626/1 እና 628/ሀ ተብሎ ተጣምሮ ተለይቶ መቅረብ መቻል አለበት፡፡

ግልፅ ብሎ ከላይ በተመለከተው መልክ ክሱ የሚቀርብ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ እርግዝናውን ማረጋገጥ እንኳን ቢያቅተው አንቀፅ 628/ሀ ወደምን  መቀየር እንዳለበት ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ ሌላ በዋነኝነት አንቀፅ 628/ሀ የመሳሰሉ ድንጋጌዎች እራሣሳቸው ለብቻቸው የሚቆሙ አይደሉም፡፡ የወንጀል ተግባሩ በዋነኝነት የሚወድቀው በሌላ የሕግ አንቀፅ ስር ነው፡፡ ከዚህ የሕጉ ድንጋጌ ላይ ሌላ ተጨማሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ነው ቅጣቱ ከሌላ የሕጉ ድንጋጌ አንፃር መታየት ያለበት፡፡ ክሱ ለዐቃቤ ሕግ፣ ለተከሣሹና ለፍ/ቤቱ ግልፅ መሆን አለበት፡፡ ጥፋተኛነትን ለማረጋገጥ ከማገዙ በተጨማሪ በቅጣት ጊዜም አስገድዶ ያስረገዘ እና ሣያስገድድ ያስረገዘ በአንድ ዓይነት መታየት የለባቸውም፡፡ ሕጉ ሆን ብሎ ነው ለያይቶ ያስቀመጣቸው፤ ወንጀልን የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎች በሚገባ መለየት አለባቸው፡፡

አንድን ተግባር ወንጀል አድርጐ ለማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ከአንድ በላይ የሕጉ ድንጋጌዎች መጠቀስ አለባቸው፤ ሊጠቀሱ ይገባል፡፡ ለምሣሌ ሠራተኛ ስርቆት ከፈፀመ የስርቆት ወንጀልን ምንነት ከሚደነግገው የወ/ሕ/አ 665/1 ጋር ተጣምሮ 669/2/መ መጠቀስ አለበት፡፡ መምህር 13 ዓመት ያልሞላትን ተማሪውን ቢደፍርና ከባድ አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጉዳት ቢያደርስባት በወ/ሕ/አ 627/1፣ 4/ሀ እና 5 ስር ተጠቃሎ መከሰስ አለበት፡፡ የማክበጃ ምክንያቶች ሲኖሩ በቅጣት ጊዜ ይታያሉ የሚለው አስተሳሰብ አሣማኝ አይደለም፡፡ ተከሣሹ በህፃኗ ላይ በደሉ ደረሰ ቢባል እንኳን አስቀድሞ አውቆት ጉዳቱ ቀላልና ከባድ መሆን አለመሆኑ ላይ አስፈላጊውን ክርክር ማቅረብ አለበት፡፡ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ እንደገና ዐቃቤ ሕግ በፊት ክሱ ላይ ያልተጠቀሰውን የሕግ አንቀፅ 627/5 ጠቅሶ ከባድ ጉዳት ነው የዕድሜ ልክ ፅኑ እስር ይወስን ብሎ ሲያመለክት ተከሣሹ ያላሰበው ስለሚሆን ከባድ አይደለም ብሎ ሊከራከር ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደገና ማስረጃ ለመስማት የሚፈቅድለት ሕግ የለም፡፡ የሂደቱን ተገማችነት ለማረጋገጥ ዐቃቤ ሕግ  ክሱን ሲያዘጋጅ አንድን ተግባር ወንጀል ያደረጉትን የሕጉን ድንጋጌዎች በጥንቃቄ አገናዝቦ ተገቢነት ና ተያያዥነት ያላቸውን ከአንድም በላይ ቢሆን ጠቅሶ ግልፅ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡

በክሱ ላይ የማስረጃ አጠቃቀስን በተመለከተ የተለያየ አሠራር አለ፡፡ ምስክሮች፣ ሠነዶችና ሌሎች ማስረጃዎች ምን እንደሚያስረዱ ለማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ላይ በግልፅ ማስቀመጥ በጉምሩክ ዐቃቤ ሕግ የተለመደ አሠራር ነው፡፡ ይህ በችሎት ሂደት ምስክሩ በቀጥታ ወንጀሉን ሲፈጽም ያየ የዓይን ምስክር ነው ወይስ በተዘዋዋሪ መንገድ ያወቀ የሚለውን ለይቶ ቢያስቀምጥ እራሱ ዐቃቤ ሕግ የችሎቱን ሂደት በቀላሉ ለመምራትና አላስፈላጊ የተደጋገመ የምስክርነት ቃልን ለመለየት ስለሚረዳ ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ ሊተገበር ይገባል፡፡ በአብዛኛው ግን የማስረጃ ዝርዝር ስር ማስረጃዎችን በቻ በመጥቀስ በግልፅ የሚያስረዱትን ሣያረጋግጡ ማቅረብ የተለመደ ነው፡፡

በረቂቁ ሕግ ላይ ከክስ አቀራረብ ጋር በተያያዘ የተደረገ መሠረታዊ ለውጥ የለም፡፡ ከክስ አዘገጃጀትና አቀራረብ ጋር በተያያዘ እያጋጠሙ ያሉና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ከግንዛቤ ውስጥ ገብተው ሕጉ ተሻሽሎ መፅደቅ አለበት፡፡

ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ክስን ማቅረብ የመጨረሻ አማራጭ አድርጐ መውሰድ አለበት፡፡ ከክስ በፊት ጉዳዩ ዕልባት ማግኘት ካለበት ይህንን አረጋግጦ መዝገቡ መዘጋት አለበት፡፡ ክስ ለማቅረብ ከወሰነም አዘገጃጀቱ ሕጉን ተከትሎ ፍትሐዊ ውሣኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ የሆነ ክስ መቅረብ አለበት፡፡

# የመወያያ ነጥቦች

1. ዐቃቤ ሕግ ክስ አዘጋጅቶ ከማቅረቡ በፊት ሊከተላቸው የሚገቡ ሂደቶች ምንድናቸው ?
2. ብቃት ያላቸውን ክሶች አዘጋጅቶ ለማቅረብ ዐቃቤ ሕግ ምን ዓይነት አሠራሮችን መከተል አለበት?
3. ክስ ላይ ማናቸውም ዓይነት ቀላል ስህተት በተገኘ ቁጥር ተሻሽሎ አዲስ ክስ መቅረብ አለበት ወይስ እንደነገሩ ሁኔታ እየታየ ቀላል ስህተቶች በፍ/ቤቱ እውቅና የተከሣሹ ወይም ጠበቃው አስተያየት ተሰምቶ እዚያው ክሱ ላይ ሊስተካከል ይገባል?
4. ክስን ከቀላል ወደ ከባድ ማሻሻል ሊከለከል ይገባል ወይ?
5. ቅጣት የሚያከብዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ በምን መልኩ ክስ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት?

## ምዕራፍ አምስት

## የወንጀል ተጠቂዎች በሚኖሩበት ጊዜ የችሎት አመራር

### አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

ይህን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ሠልጣኞቹ

1. በወንጀል ተጠርጣሪዎች እና በወንጀል ተጠቂዎች መካከል ያሉ ተነፃፃሪ መብቶችን ይገነዘበሉ
2. የወንጀል ተጠቂዎችን የሥነልቦናና ማህበራዊ ፍላጎቶች መሰረት ያደረገ የፍትህ አመራር ዘዴን ይለያሉ

3. ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ

**ዝርዝር ዓላማዎች፡-**

በምዕራፉ የተመለከቱትን ክፍለ ትምህርቶች ከተከታተሉ በኋላ ሠልጣኞች፡-

1. በወንጀል ተጠርጣሪዎችና በወንጀል ተጠቂዎች መካከል ያሉ ተነፃፃሪ መብቶችን ይለያሉ
2. የወንጀል ተጠቂዎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው ይለያሉ
3. የወንጀል ተጠቂዎችን የሥነ ልቦና እና ማህበራዊ ፍላጎቶችን ይለያሉ
4. እነዚህ ፍላጎቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ዘዴ ይለያሉ በመልመጃዎች ላይ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## ክፍል አንድ

## የወንጀል ተጠርጣሪዎች እና የወንጀል ተጠቂዎች ተነፃፃሪ መብቶች

ሕጎች በአጠቃላይ ከይዞታቸው አንፃር ዋና ሕጎች እና ቅፅል ሕጎች (Substantive and Adjunctive laws) ተብለው እንደሚከፈሉ ከዚህ ቀደም ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከወንጀል አንፃር ያሉ ዋና ሕጎች ሕግ አድርግ ያለውን አለማድረግ ወይም አታድርግ ያለውን ማድረግ ሊያስቀጣ እንደሚችል የሚደነግጉባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ከወንጀል አንፃር ያሉ ዋና ሕጎች በወንጀል ተጠርጣሪ ወይም በወንጀል ተጎጂ መካከል ልዩነት የሚያደርጉ ናቸው ተብለው የሚወሰዱ አይሆኑም፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ ዋና ሕጎች ዓላማ አንድን ወገን መሠረት ያደረገ ሳይሆን ለአጠቃላይ ማኅበረሰቡ በመርህነት/ገዢ ሕግነት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ፅንሰ ሃሳቦች ማስተላለፍ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ዓላማና ግብ ለምሳሌ ያህል ብንመለከት "የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግሥት፣ የሕዝቦቹን፣ የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" ይላል (አንቀጽ 1)

የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ እንደሚያስረዳው ትኩረቱ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሲሆን ፤ አጥፊም ሆነ ተጎጂ ከመኖራቸው በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውን ወይም የማይገባቸውን ነገሮች አስቀድሞ በማሳወቅ ላይ ያተኮረ እንደመሆኑ ተደራሽነቱ (የሕግ መተላለፍ እስከሚፈፀም ድረስ) ለአጥፊም ሆነ ለተጎጂ እኩል ሆኖ ይስተዋላል፡፡

የወንጀል ሕጉ ወደሚፈፀምበት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች በምንመጣበት ጊዜ ዋናው ሕግ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሊያስቀጡ ይችላሉ ብሎ ያስቀመጣቸው ጉዳዮች ተጥሰው በሚገኙበት ወቅት የሚወሰደውን ቀጣይ እርምጃ የሚመራበትን ሥርዓት የሚደነግግ እንደመሆኑ ለወንጀል ተጠርጣሪዎችም ሆነ ለወንጀል ተጠቂዎች ሊከበሩ የሚገቡ መብቶች ተካተውበት እናገኛለን፡፡

## 1.1. የወንጀል ተጠርጣሪዎች መብቶች

በበርካታ የዓለም አገራት እንደሚስተዋለው ከሕገ መንግስት ጀምሮ በዝርዝር የሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ ጥበቃ የሚደረግላቸው በርካታ የወንጀል ተጠርጣሪዎች መብቶች አሉ፡፡ ለዚህም ቢያንስ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው አታድርግ የተባለውን በማድረጉ ወይም አድርግ የተባለውን ባለማድረጉ ከሕጉ ጋር ችግር ውስጥ የገባው ያው ተጠርጣሪው እንደመሆኑ በሂደት የመብት መጣስ ሊያጋጥመው የሚችለውም ራሱ ተጠርጣሪው ነው የሚለው እሳቤ ሲሆን፤ ሌላኛው ነጥብ የኃይል ሚዛንን የሚመለከት ነው፡፡ እንደሚታወቀው የወንጀል ድርጊት በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ደህንነት ላይ የተፈፀመ ተደርጐ ከሚወሰድበት እሳቤ በመነሳት በአብላጫው የወንጀል ጉዳዮች እንደግል ተበዳይ ሆኖ የሚከራከረው መንግስት/ዐቃቤ ሕግ ሲሆን፤ መንግስት ካለው አቅም አንፃር በወንጀል ተጠርጣሪው መብት ላይ ሊያሳድረው የሚችለውን ጫና ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ ይታመናል፡፡

በአገራችን ሕጎች መሰረትም በሕገ መንግስቱም ሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ውስጥ የተካተቱ በርካታ የተጠርጣሪዎች መብቶች አሉ ከችሎት አመራር አንፃር አለፍ አለፍ እያሉ ለመመልከት ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

### ሀ. በፍርድ ቤቶችና በሌሎች የዳኝነት አካላት ፊት በእኩልነት መታየት

ይህ መሠረታዊ መብት አንድ ተጠርጣሪ በዘሩ፣ በኃይማኖቱ፣ ፆታው፣ የሀብት መጠኑ ወ.ዘ.ተ ልዩነት ሳይደረግበት ከሌላው ተከራካሪ ወገን እኩል በፍርድ ሚዛን ላይ መቀመጥ መቻሉን የሚመለከት መብት ነው፡፡

### ለ. ንፁሕ ሆኖ የመገመት መብት

ማንኛውም ተጠርጣሪ ከፍርድ በፊት ልክ እንደወንጀለኛ መቆጠር እንደሌለበት እና በተከሰሰበት ወንጀል ነፃ ሆኖ የመገመት መብት እንዳለው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 20/3/ ተደንግጓል፡፡

ሐ. **የተፋጠነ ፍርድ የማግኘትና በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብት**

የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኂላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመዳኘት መብት አላቸው (የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 20/1/)

መ. **ማስረጃን የማወቅ/ ምሥክሮትን የመጥራትና የመመርመር መብት**

የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማናቸውም ማስረጃ መመልከትና የቀረቡባቸውን ምሥክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምሥክሮቻቸው ቀረበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው (የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20/4/

ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች በችሎት አመራር ወቅት ሊከበሩ የሚባቸው የተጠርጣሪዎች/ተከሣሾች መብቶች አሉ፡፡

ለምሣሌ፡- - በሰንሰለት ሳይታሰሩ የመቅረብ መብት (የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 127/2/ የኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 18/1/

- ነፃ የተርጓሚ አገልግሎት የማግኘት መብት
- በመረጡት ጠበቃ የመከራከር/ ጠበቃ እንዲቆምላቸው የመጠየቅ መብት
- በዋስ የመለቀቅ መብት
- ራስን ከመወንጀል የመጠበቅ መብት
- የይግባኝ መብት

ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## 1.2. **የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች**

ስለ ወንጀል ተጠቂዎች በሚነሳበት ወቅት ጎልቶ የሚወጣ አንድ ጥያቄ አለ፡፡ ይኸውም የወንጀል ተጠቂ ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በተለያዩ ምሁራንና የአመለካከት ዘርፎች ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ በአጠቃላይ ለመረዳት እንደሚቻለውም እንደወንጀሉ ሁኔታ የወንጀል ተጠቂ የሚለው ፅንሰሃሳብ የተለያዩ አካላትን ሊያካትት የሚችል ነው፡፡

ለምሣሌ ያህል በወንጀል ጉዳዮች ላይ ዐቃቤ ሕግ ተጠቂ ሆኖ በተሟጋችነት መቅረቡ በአንድ የወንጀል ድርጊት አጠቃላይ ተጠቂው ማህበረሰቡ በጠቅላላው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

በተጨባጭም አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶች አጠቃላይ የማህበረሰቡን ቁጣ ሲቀሰቅሱና አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ህብረተሰቡ በሰላማዊ ሰልፍና በተለያዩ መንገዶች ስሜቱን ሲገልፅ የሚስተዋልባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ይህም ከግል ተበዳይ ሌላ በአንድ የወንጀል ድርጊት የአጠቃላይ ህብረተሰቡ ሰላማዊ ሕይወት ሊናጋ እና አንድ ማህበረሰብ እንደማህበረሰብ የወንጀል ተጠቂ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ የሚያመለክት ነው፡፡

የወንጀል ተጠቂ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ጠበብ አድርገን ስንመለከተው ደግሞ በመጀመሪያ ረድፍ የምናገኘው በወንጀል ምክንያት ቀጥተኛ ሰለባ የሚሆኑትን የግል ተበዳዮች ወይንም ደግሞ የግል ተበዳዮችን ቤተሰቦች ነው፡፡ አንድ የሥርቆት ወንጀል ቢፈፀም ሥርቆት የተፈፀመበት አካባቢ ህብረተሰብን ሰላማዊ ኑሮ መደፈር ከማሰብ ባሻገር ንብረቱ የተሰረቀበት ግለሰብ ንብረቱን በማጣቱ የሚደርስበት ቁሳዊ ጉዳት የግል ህይወቱ በመደፈሩ የሚደርስበት ሞራላዊ ጥቃት ሊታሰብ የሚችል ነው፡፡ በተመሳሳይ አንድ የግድያ ወንጀል ቢፈፀም የሟች ቤተሰቦች ላይ የደረሰው ጥቃት በህብረተሰቡ ሰላማዊ ኑሮ ላይ ከሚደርሰው ጥቃትና ተፅእኖ ተለይቶ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

የወንጀል ተጠቂዎችን መብት ጠለቅ ብለን በምናይበት ወቅት በተለይ ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ምርምሮችን ያስነሳ እና መደበኛውን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ጥያቄ ውስጥ የከተተበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ ጀምሮ እየሰፋ የመጣው የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች እንቅስቃሴ (Victims' Right movement) በመደበኛው የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ላይ ከሚሰነዝራቸው ትችቶች ዋነኛው "መደበኛው የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ለወንጀል ተጠቂው (ለተጎጂው) ምን ይደረግለት ከሚለው ጥያቄ ይልቅ አፅንኦት ሰጥቶ የሚቆመው ተጠርጣሪው ወይም አጥፊው ምን ይደረግ የሚለው ነጥብ ላይ ነው" የሚለው ነው፡፡

ስለዚህም እንደ እንቅስቃሴው ዕምነት መደበኛው የወንጀል ፍትህ ሥርዓት የወንጀል ተጠቂዎችን ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ፍላቶጎቶች የሚመልስ አይደለም፡፡ በዚህም የተነሳ በወንጀል ፍትህ ሥርዓት አካሄድ ሂደት ውስጥ የወንጀል ተጎጂዎች ለዳግመኛ ተጎጂነት (Secondary victimization ) ይጋለጣሉ፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ የወንጀል ተጠቂዎች ያላቸው ወይም ሊኖራቸው የሚገባ መብቶች የትኞቹ ናቸው? የሚል ነው፡፡

ለወንጀል ተጠቂዎች ሊጠበቁላቸው ይገባል ተብለው ከሚታመኑ የመብት ጥያቄዎች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ሀ. **የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብት**

አንድ ተጠርጣሪ በቀረበበት የወንጀል ክስ መብቱ አላአግባብ ተገድቦ እንዳይቆይ የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብቱ መጠበቅ ያለበትን ያህል በወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎችም እንዲሁ ለቀጣይ ህይወታቸው ሰላማዊ ዋስትና ለደረሰባቸው የወንጀል ጥቃት አፋጣኝ ፍትህ ይሻሉ፡፡

ለ. **የመደመጥ/የመሰማት መብት**

የወንጀል ተጠቂዎች መልስ የሚሹላቸው ብዙ ጥያቄዎች ይኖሯቸዋል፡፡ ለምን ጥቃቱ በእኔ ላይ ደረሰ ? ጥቃቱ በእኔ ላይ እንዳይደርስ ምን ማድረግ ነበረብኝ ? ወደፊትስ ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይደርስብኝ ምን ዋስትና አለኝ ? ወ.ዘ.ተ የሚሉት ጥያቄዎች በወንጀል ተጠቂዎች አእምሮ የሚመላለሱ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የደረሰባቸው የወንጀል ድርጊት ስላሳደረባቸው ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጠባሳ ለመደመጥ ይሻሉ፡፡ ስለሆነም በሕግ ፊት ቀርበው መደመጥ ይፈልጋሉ፡፡

ሐ. **ካሣ የማግኘት መብት**

ለደረሰባቸው ቁሳዊ፣ ሞራላዊና አካላዉ ጥቃት የወንጀል ተጎጂዎች ካሣ የማግኘት መብት ይህንንም ለማረጋገጥ የህግ ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

መ. **ጥበቃ የማግኘት መብት**

በአጠቃላይ በወንጀል ጉዳይ ምሥክር ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች ሊጠበቅላቸው ከሚገባ መብት አንዱ በወንጀል ጉዳይ ምሥክር ሆነው በመቅረባቸው ወይም ሊቀርቡ በመቻላቸው የተነሳ ሊደርስባቸው ከሚችል ማናቸውም ዓይነት ጥቃት የመጠበቅ መብት ነው የወንጀል ተጎጂዎችም የደረሰባቸውን ጥቃት ለመመስከር በመቻላቸው ሊደርስባቸው ከሚችል ዛቻ ወይም አካላዊና ቁሳዊ ጥቃት የመጠበቅ መብት አላቸው፡፡

ሠ. **ከዳግም ተጎጂነት (Secondary Victimization ) የመጠበቅ መብት**

የወንጀል ተጎጂዎች ምሥክር ሁነው የሚቀርቡ በመሆናቸው ወይም በመቅረባቸው ሊደርስባቸው ከሚችል ጥቃት ባሻገር በተጎጂነታቸው ራሱ ሊያጋጥማቸው የሚችል ማህበራዊ መሰናክል እንዲሁም ጥቃታቸውን በአደባባይ ለመግለፅ የሚያጋጥማቸው አእምሮአዊ ጫና እንዲሁም በፍርድ ሂደት ሊያጋጥሙዎቸው ከሚችሉና መንፈሣቸውን በማቁሰል ለዳግም ተጎጂነት ከሚዳርጓቸው ሁኔታዎችም ጥበቃ ያሻቸዋል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

* ከዚህ በለይ የተጠቀሱና የተጎጂዎች መብቶች ተብለው የተጠቀሱ ነጥቦች በኢትዮጵያ ሕጎች ምን ያህል የተሸፈኑ ናቸው?

## ክፍል ሁለት

## የወንጀል ተጠቂዎችና የችሎት አመራር

### ሀ. ተጠቂዎች በችሎት እንዲቀርቡ እና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል

ስለ ወንጀል ተጠቂዎች በሚታይበት ጊዜ የችሎት አመራርን በፍርድ ሂደት ከሚደረገው የግራ ቀኝ ክርክር ሰፋ አድርጐ ማየት ይጠበቃል፡፡ በችሎት በሚደረገው ክርክር ለጉዳዩ አስረጂ ተብለው በግራ ቀኙ የተቆጠሩ አለበለዚያም ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በተጨማሪነት ከሚቀርቡ ውጪ አስረጁ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የችሎት አመራርን ስናስብ የወንጀል ተጎጂዎች እድሉን አግኝተው መሰማት መቻላቸውንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በተለይ ደግሞ ተጎጂው የግል ተበዳይ ሆኖ በምስክርነት ካልቀረበ በስተቀር በችሎት በሚደረገው ክርክር ተሳትፌ የሚሆንበት ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ ለምሳሌ፡- ልጃቸው የተገደለባቸው ወለጆች ልጃቸው ሲገደል ያዩ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን በችሎት ቀርበው ሲሰጡ ከመመልከት ውጪ ራሳቸው ቀርበው በልጃቸው መገደል የደረሰባቸውን ሞራላዊና ቁሳዊ ጉዳት እንዲያስረዱ እድል ላይሰጣቸው ይችላል፡፡

በእርግጥ ወላጆቹ ወንጀሉ ሲፈፀም እስካልተመለከቱ ድረስ በችሎት በተያዘው ዋናው ጉዳይ ላይ እነሱ የሚሰጡት ቃል የሚያሳድረው ተፅዕኖ ዝቅተኛ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በመጨረሻ ለሚሰጠው ሚዛናዊ ውሣኔ የወላጆቹ ቀርቦ መመስከር ጠቀሜታ ሊኖረው ከመቻሉ ባሻገር በዋነኝነት ወላጆቹ መደመጥ በመቻላቸው ብቻ በልጃቸው ሞት የተሰማቸውን ህመም በእጅጉ ሊቀንሰው እንደሚችል መታሰብ አለበት፡፡

በሌላ በኩል ከፍ ሲል የተጠቀሱት ወላጆች በምሥክርነት ተቆጥረው ቀርበው መስክረው ቢሆን እንኳን አስረጂነታቸው በዐቃቤ ሕግ በኩል ለሚቀርበው ዋና ጥያቄ ብቻ ስለሚሆን ከዚያ በኋላ በሚኖረው የችሎት ሂደት ምንም ዓይነት ተሳትፎ አይኖራቸውም፡፡ ለምሣሌ ተከሣሽ ያቀረበው መከላከያ ሃሰተኛ መሆኑን ቢያውቁ ዝም ብለው ተነስተው ይህንኑ ለችሎቱ ማሳወቅ የሚችሉበት ሥርዓት

የለም፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ጉዳዩን በዋነኝነት የያዘው ዐቃቤ ሕግ የችሎት ሂደት እስከሚያልቅ ድረስ ከወንጀል ተጠቂዎች ጋር በቅርብ በመስራት በችሎት ሂደት መደመጥ መቻላቸውን ማረጋገጥ እንዳለበት ነው፡፡

ለ. <u>በዝግ ችሎት ጉዳይን ማየት</u>

አንዳንድ የወንጀል ጉዳዮች የሚያሳድሩት የሥነ ልቦና ጫና እጅጉን የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡ በእንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ተጎጂች በግልፅ ችሎት ቀርበው እንዲመሰክሩ ማድረግ ለተጨማሪ ስነ ልቦናዊ ቀውስ ሊዳርጋቸው የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚፈጥር አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት ሁሉ ዐቃቤ ሕግ ፍርድ ቤቱ የምሥክርነት ቃላቸውን በዝግ ችሎት እንዲሰማ ማሳሰብ መቻል አለበት፡፡

ሐ. <u>ለዳግም ተጎጂነት ከሚዳረጉ ጥያቄዎች መጠበቅ</u>

የወንጀል ተጎጂዎች የምሥክርነት ቃላቸውን በሚሰጡበት ወቅት በዋና ጥያቄ፣ በመስቀለኛም ሆነ በማጣሪያ ጥያቄ ሞራላቸውን ሊነካና ለዳግም ተጎጂነት ሊዳርጋቸው ከሚችል ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ሊጠበቁ ያሻል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. የተጎጂዎችን/ ምሥክሮችን በዝግ ችሎት መስማት ከተጠርጣሪዎች በግልጽ ችሎት የመዳኘት መብት ጋር አነፃፅረው ይመልከቱ
2. የወንጀል ተጎጂዎችን ለዳግም ጥቃት ላለመዳረግ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ ?

[illegible]

ቀን [illegible] 92

ለወረዳ 17 ፖሊስ ጣቢያ

<u>አዲስ አበባ</u>፣

የዐ/ሕ/ወ/ቁ.3291/91

<u>የወ177/ወ/ቁ.199/92</u>

ነበር አበባ በተከሰሰበት ወንጀል የተጻፈው የምርመራ መዝገብ በቁጥር 537/ወ/2/91 በ12/12/91 በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት ደርሶን ተመልክተነዋል::

የክሱ ፍሬ ነገር በከሣሽነት ቀርባ ቢመለከተው አያን አሊ መሠረት ተከሣሽ ወደ ሰዑዲ አገር እልክሻለሁ [illegible] 900 ዶላር አታሎ ወስደዋል በማለት በሰጠችው ቃል መሠረት የተጻፈ መዝገብ ነው::

መዝገቡን እንደመረመርነው ክስ ከመመስረቱ በፊት ሊሟላ የሚገባ ነጥብ አግኝተናል ይህም ከሣሽ ሆና ያቀረበችው ገለሰብ ተወስዶበታል የምትለው የውጭ አገር ገንዘብ ወደ አገር ውስጥ ስታስገባ በተገባው የመንግስት አካል ማስመዝገቧንና ከተመዘገበም ማስረጃ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ተመልሶ መዝገቡ እንዲላክልን የምርመራ መዝገቡን ______ገጽ እንደያዘ የላክን መሆናችንን እናስታውቃለን::

[illegible]

/ጕ.ል

ለወረዳ 7 ፖሊስ ጣቢያ

[illegible]

አ/አበባ

[illegible]

[illegible]

ቁጥር ፡ ጸ/ዐ/ወ/ዐ/2274/2209/90

ቀን ፡ 21/7/96

የጸ/ዐ/ዐ/ወ/ቁ.2209/90

የወ/7/7/ም/መ/ቁ.1066/90

ሙሉጌታ ካሣሁን በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የተጣራው የምርመራ መዝገብ በቁጥር 7/ወ7/7351/90 በ6/11/90 ዓ.ም በተጻፈ ሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት የተላከልን ደርሶን ተመልክተነዋል፡፡

በተከሳሽ ላይ የቀረበውን የምርመራ መዝገብ መርምረን እንደተረዳነው ተከሳሽ በ22/03/89 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በወረዳ 7 ቀበሌ 28 ልዩ ቦታው ቀቢላ አካባቢ የግል ተበዳይ ያረጋል ረታ ንብረት የሆነውን አንድ 24 እና 27 የሆነ የጎማ መፍቻ ሰርቆ ወስዷል በሚል የቀረበ ክስ ነው፡፡

በተከሳሽ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.27/2 መሠረት በሰጠው የተከሳሽነት ቃል የወንጀሉን ድርጊት መፈፀሙን አምኖ ቃል ሰጥቷል፡፡

በተከሳሽ ላይ ለቀረበው ክስ ተከሳሽ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያስረዳ ማስረጃ የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በተከሳሽ ላይ በግል ተበዳይ አማካኝነት ክስ የቀረበበት ቢሆንም እንደክሱ አቀራረብ ተከሳሽ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ባለመቀረቡ ምክንያት በተከሳሽ ላይ ክስ መመሥረት ስለማይቻል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.42/1/ሀ መሠረት በተከሳሽ ላይ ክስ እናቋርጠም በማለት ወስነናል፡፡ በመሆኑም ተልኮልን የነበረውን የምርመራ መዝገብ በውስጡ 10 ገጽ አባሪ እንደያዘ መልሰን የላክን መሆናችንን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የአ/[illegible]/ቁ/ጽ/ቤት

ኃላፊ

ግልባጭ ፡

- ለአ/አ/አስ/የፍ/ሚ/ር/ተ/ጽ/ቤት

አ/አበባ

/ፍስ

የክሱ ጭብጥና የማስረጃው ሁኔታ ከላይ በአጭሩ እንደተገለፀው ነው በአጠቃላይ የምርመራ መዝገቡን እንደመረመርነው ተከሳሾችን ጥፋተኛ አድርጎ ክስ ለመመሥረት ከጥርጣሬ ውጭ ተጨባጭ እና በቂ ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 42/1/ሀ መሠረት በተከሳሾቹ ላይ ክስ ለመስረተብቸው አይገባም በማለት ውሳኔ ተሰጥቶን የነበረውን የምርመራ መዝገብ በውስጡ 15 ገጽ እንደያዘ መልሰን የላክንላችሁ መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

መንገስቱ አየለ
የአ/ዐ/ፍ/ሚ/ር/ቀ/ጽ/ቤት
ኃላፊ

ግልባጭ

- ለአ/አ/አበ/የፍ/ሚ/ር/ተ/ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፍትሕ ሚ/ር የፌ/ዐ/ሕግ ...
የምኒልክ ምድብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ቁጥር 3384/96 - ቦ-70/96
ቀን 3-9-96

ለወረዳ 15 ፖሊስ ጣቢያ

<u>አዲስ አበባ</u>

የም/ም/የፍ/ሚ/ቅ/ጽ/ቤት መ/ዝ/ቁ 70/96
<u>የወረዳ 15 ፖሊስ ወ/መዝገብ ቁ/3265/96</u>

አቶ በረከ ሙሉጌታ ተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት የተጣራው የምርመራው ምርመራ መዝገብ በቁጥር ዐ/ሕግ/03/20089/96 ሚያዝያ 16 ቀን 1996 ዓ.ም በተጻፈ ሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት የተላከልን ደርሶን ተመልክተናል።

በተከሳሽ ላይ የቀረበው የምርመራ መዝገብ መርምረን እንደተረዳነው ተከሳሽ በ5/8/1996 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 11:00 ሰዓት በወረዳ 15 ቀበሌ 18 ልዩ ቦታው አጣና ገበያ አካባቢ የግል ተበዳይ አቶ መንገሻ ሸገገካን ድንጋይ ወርውሮ በቀኝ ጉልበታቸውና የግራ ተረከዛቸው ላይ በመምታት ጉልበታቸው እንዲደማና ያፈጠው እግ ሊያብጥ አድርገዋል በማለ የቀረበ ክስ ነው።

ተከሳሽ ቀረበበት ክስ የሰጡት የተከሳሽነት ቃል የተከሰሰበትን የወንጀል ድር ጊት አለፈጸምኩም በሰዓል በማለት የተከሳሽነት ቃል ሰጥተዋል።

እንደ ክሱ አቀራረብ የሚያስረዱ የሕግ ምስክሮች አለ ቀረበም የግል ተበዳይ በሰጡት ቃል ማስረጃ የለኝም በሰዓል እንጂም ምስክሮች አለ ቀረበም የግል ተበዳይ በሰጡት ቃል ማስረጃ የለኝም በሰዓል እንጂም ምስክር አለ ቀረበም።

ከዚህ በመነሣት እንደ ተከሳሽ ሊከሰስ የሚችለው ፈጸመ ለተባለው የወንጀል ድርጊት በማያጠራጥር እና በማያሻማ ሁኔታ ድርጊቱን ለመፈጸሙ የሚያስረዳ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ ነው። በዚህም መሰረት ተከሳሽ ወንጀሉን ለመፈጸማቸው የሚያስረዳ

.../2

በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ የክንያቱ ተከሣሾች ላይ ክስ መመስረት ስለማይቻል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/42/1/ሀ መሠረት ክስ [illegible] በማለት ወስኛለሁ። በመሆኑም ተሰብስቦ የነበረው የምርመራ መዝገብ በፖሊስ____ገጽ እንደዘጋ ወሰነን የከሣሾች መሆኑን እናሳውቃለን።

የፍትሕ ሚ/ር

ከሰላምታ ጋር

[illegible]

የም/ቦ/የና/ወ/ር/ጉ/ጽ/ቤት

ዓ ቃ ሬ

ግልባጭ ፦

ለአዲስ አበባ አስተዳደር
የፍትሕ ቢ/ር/ቀ/ጽ/ቤት
አዲስ አበባ